**መግቢያ...............................................................................................2**

**1. የስድሳዎቹ የኢትዮጵያ ፖለቲካና ቀዝቃዛው ጦርነት...............................4**

**2. የስድሳዎቹ ፖለቲካ የወለዳቸው የአደረጃጀት መልኮች.............................8**

**3. የደርግ መውደቅና የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ማክተም.........................13**

**4. የእስከሁኑ ሕብረቶችና ችግሮቻቸው..........................................................18**

**5. ሕብረት አሁንም ይቻላል.........................................................................23**

**6. ማጠቃለያ...........................................................................................35**

# መግቢያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል እውቅና አግኝቶ ይፋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ከተጀመረ አስራ አምስት ዓመታት አልፎታል:: የዚህ እርምጃ አላማ ፖለቲከኞች አቋሞቻቸውን በፕሮግራምና በፖሊሲ መልክ ቀርፀው፣ ስብሰባቸውን በፓርቲ መልክ አዋቅረው፣ አማራጫቸውን ለህዝብ የሚያቀርቡበት ነፃ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው፣ ሀሳቦቹ በህዝባዊ መድረኮች በነፃ እንዲንሸራሸሩ ከተደረገ በኋላ ህዝቡ ይበጀኛል ያለውን በምርጫ እንዲወስን ለማድረግ ነው::

ፖለቲከኞች ወይም ፖለቲካዊ ፓርቲዎች የሚያቀርቡለትን የተለያዩ አማራጮች ህዝቡ ሰምቶ እና በነሱ ዙሪያ መክሮ፣ በየወቅቱ በሚደረጉት ምርጫዎች ይበጀኛል ያለውን መርጦ ለስልጣን እንዲበቃ ማድረግ በኢትዮጵያ ታሪክ ተንሰራፍቶ የቆየውን ስልጣንን በኃይልና በደም መፋሰስ የመያዝና የማስጠበቅ ታሪክ መቋጫ ያስገኛል፤ የኃይልና የጉልበት መንገድ አብቅቶ በሃሳብ በልጦ በመገኘት ብቻ ስልጣን የሚያዝበት ሁኔታ ይፈጥራል፤ ይህ ሲሆን ለጦርነት እና በጦርነት ይባክን የነበረው የሀገሪቱ ሀብትና እውቀት ለሀገር ግንባታና ልማት ይውላል፤ በዚሁ መንገድም ስላም፣ ቀጣይነት ያለው የሀገር እድገትና ልማትን ያመጣል የሚል ተስፋ ነበር::

የሽግግር ዘመኑን ጨምሮ ኢህአዴግ በስልጣን ላይ 17 ዓመታት ቆይቷል:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ህገ መንግስት ፀድቆ እስካሁን ድረስ ሶስት ብሄራዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል:: ይሄም ሆኖ ግን ኢህአዴግን በሌላ ፓርቲ ለመተካት አልተቻለም:: ይህ ሊሆን የቻለው ኢህአዴግ ብልሹ ፖሊሶዎች ስላልነበሩት ወይም ህዝቡ ኢህአዴግ እንዲቀየርለት ስላልፈለገ አይደለም::

ኢህአዴግን ለመቀየር ያልተቻለው በሁለት ምክንያት ነው:: አንደኛ ኢህአዴግ ራሱ ባወጣቸው ህጐች አማካኝነት እርሱን በሌላ ፓርቲ ለመቀየር እጅግ አስቸጋሪ እንዲሆን በማድረግ ለተፎካካሪዎች አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮባቸዋል፣ ተቋሞቹንም በራሱ ፍላጎትና በራሱ ምስል ቀርጿቸዋል:: ሌላኛው ምናልባትም ዋና ሊባል የሚቻለው ችግር ደግሞ በተቃዋሚዎች በኩል ያለ የስክነትና የብስለት ችግር ነው:: በስራ ላይ ያለው እና ተመዝግቦ በመድረክ ሳይታይ ከስሞ የቀረው ተለይቶ ባይታወቅም እስካሁን ድረስ በፓርቲነት የምዝገባ ሰርተፍኬት የወሰዱ ፓርቲዎች ብዛት ሲታሰብ ግን ሰማንያ ዘጠኝ መድረሱን ምርጫ ቦርድ በቅርቡ ከሰጠው መግለጫ ለመገንዘብ ተችሏል:: ባለፉት ሶስት ምርጫዎች እንደታየው ግን በ97ቱ ምርጫ ቅንጅት አዲስአበባን ካሸነፈበት ክስተት በስተቀር በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ኢህአዴግን አሸንፎ ስልጣን ለመያዝ የበቃ ተፎካካሪ ፓርቲ አልተገኘም::

የጐፈረ ሁሉ ጀግና አይወጣውም እና ፓርቲ ነኝ ያለው ሁሉ እርባና ያለው ፓርቲ ይወጣዋል ማለት ስለአልሆነ ስንዴን ከእንክርዳዱ ለመለየት ጊዜ ማስፈለጉ የማይቀር ቢሆንም ይህንን ለማሳካት ግን አስራ አምስት ዓመት አይጠይቅም፡፡ ከዚህ ሁሉ ስብስብ እርባና ያለውና ዓይን የሚሞላ የተፎካካሪ ስብስብ ለመውጣት ያለመቻሉ ዋና ምክንያት የብስለትና የብቃት ማነስ ነው ሊሆን የሚችለው፡፡ በዚህ ምክንያት በጋራ ለመስራት የሚያስችሉትን የጋራ አቋሞች ለማንጠር አለመቻል፣ ይባስ ብሎ ደግሞ ልዩነቶችን አቻችሎና አቀራርቦ አማካይ ሁኔታ በመፍጠር ፈንታ ልዩነቶቹን እያደመቁ እኔን ምረጡ እኔን ልዩ የሚያደርገኝ ይህ ነው ብሎ በልዩነት ላይ መንጠልጠል ገኖ ይታያል፡፡

ይህ ሲባል የመተባበር እና አብሮ የመስራት አስፈላጊነት ግንዛቤ አልተወሰደበትም ማለት አይደለም፡፡ እየተበታተኑ በሄዱ ቁጥር የህዝቡን ተስፋና አመኔታ ማጣት እንደሚያስከትል፣በሀገራችንም የፖለቲካ ለውጥ የማምጣት እድሉ ሩቅ እንደሚያደርገው ግንዛቤ እያገኘ ሄዷል፡፡ ከህዝቡ በኩልም ወይ ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ የሚል ጥያቄ ሲቀርብ ቆቷዋል፡፡ ፖለቲከኞቹም የመተባበር አስፈላጊነት ስለተገነዘቡ በርከት ያሉ የመተባበር ሙከራዎች አካሂደዋል፡፡ በዚህ ሂደት የሰመሩ ትብብሮች አልነበሩም ባይባልም ይበልጥ ጎልቶ የታየው ግን ተባብሮ እንደገና የመበታተኑ ዝንባሌ ነው፡፡

ከዚህ በፊት የተደረጉት የመተባበር ሙከራዎች አብዛኛዎቹ ባለመሳከታቸው ወደፊት የሚካሄዱት የህብረት ሙከራዎች ዕጣ ፈንታም እንደዚሁ ይሆናል ማለት ግን አይደለም፡፡ ፖለቲከኞቹ፣ ካልተሳኩት ሙከራዎች ልምድ አግኝተዋልና ወደፊት የሚመጡት ህብረቶች ባለፈው ልምድ በልፅገው ስኬታማ የመሆናቸው እድልም አለና ወድቀት ይመጣል ተብሎ ከመሞከር መቦዘን አይገባም፡፡ ስኬት ላይ እደርሳለሁ የሚል ሰው በሙከራ ሂደት ወድቀት ሊያጋጥም እንደሚችል ካልተገነዘበና ከውድቀትም ለመማር ግን ደግሞ ወድቆ ለመነሳት ዝግጁ እስካልሆነ ድረስ ውጤቱና ስኬት ላይ መድረስ አይቻለውም፡፡ ወደፊት የተሻለ ትብብር ጋ መድረስ ይቻላል ከሚል እምነት በመነሳትም መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ የሚል የምክክር መድረክ ተጀምሯል፡፡

ይሄ መድረክ ሕብረት አይደለም፡፡ ህብረት ለመፍጠር ይቻላል ከሚል ተስፋና እምነት የመነጨ ጅምር ነው፡፡ እዚያ ጋ ለመድረስ ግን ላለመተባበር ምክንያት የሆኑትን ዋና ዋና ጉዳዬች አንስቶ የመድረኩ አባላትም ሆኑ ከመድረኩ ውጭ ያሉ ፓርቲዎች በተነሱት ጉዳዮች ላይ ያላቸው አመለካከት እንዲለዋወጡ፤ የጋራ የሆነው ነጥሮ እንዲወጣ ለማድረግ፣ ልዩነቶቹንም ለማቀራረብ እና ለማቻቻል የሚቻልበት ሁኔታ

ለማመቻቸት፤ ይህንንም በማድረግ የሰመረ ህብረት እና ትብብር ለመፈጠር የሚቻልበትን ሁኔታ ለማየት ነው ይህ መድረክ የተፈጠረው::

ለዚህም ሲባል በመነሻነት በርካታ አጀንዳዎች ለመወያያ ተመርጠዋል:: ለዚህ ፅሑፍ መነሻ የሆነውና የተፎካካሪዎች የሕብረት ጥያቄ የሚለውም አንድ አጀንዳ ነው:: በዚህ ፅሑፍ ውስጥ፣ ባለፉት ሰላሳና እና አርባ ዓመታት በኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ የታዩት ፖለቲካዊ ልዩነቶች እና ከነዚህ ፖለቲካዊ ልዩነቶች ጋር በተያያዘ የታዩት የአደረጃጀት ሞዴሎች ይዳስሳሉ:: በእነዚህ ፖለቲካዊ ልዩነቶችና የአደረጃጀት ሞዴሎች ላይ ጫና ያሳረፉ ተንዳኝ ፖለቲካዊ ክስተቶችም ይቃኛሉ:: ይህንን መነሻ በማድረግ አሁን ያለው ሁኔታና ወደፊት ህብረት ይኖር ዘንድ መታሰብ ያለባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት የዚህ ፅሑፍ አዘጋጅ የግል አስተያየት ይቀርባል::

## 1. የስድሳዎቹ የኢትዮጵያ ፖለቲካና ቀዝቃዛው ጦርነት:-

በስልጣን ላይ ያለውን ወገን ለመቃወም ህጋዊ እውቅና አግኝቶ መንቀሳቀስ የተጀመረው የደርግ ስርዓት ከወደቀ በኋላ ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ተደራጅቶ በስልጣን ላይ ያለውን ወገን መቃወም የቆየ የታሪካችን አንዱ ገፅታ ነው:: ይህም ሆኖ የሃገራችን ፖለቲከኞች ዘመኑ በሚጠይቀው መልኩ ተደራጅተው መንግስትን መቃወም የጀመሩት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከስድሳዎቹ ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል:: ይፋዊ እና ህጋዊ ተቃውሞ ለማድረግ የሚያስችል ማእቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት በዛን ወቅት መንቀሳቀስ የጀመሩት ፖለቲካዊ ድርጅቶች/ስብስቦች ተቃውሟቸውን ያራምዱ የነበሩት በህቡእና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ነበር:: ::

በዚያን ወቅት ወደ መድረክ የመጡት ድርጅቶች ያኔው ለያዙዋቸው አቋሞች፣ በመሀከላቸው ለተከሰቱት ልዩነቶች እና ልዩነቶቻቸውን ያስተናገዱባቸው ስልቶች ይዘት ላይ ጫና ያሳረፉ ሁለት ምክንያቶች ነበሩ ለማለት ይቻላል::

አንደኛው ያኔ በሀገራችን የነበሩት አንገብጋቢ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በወቅቱ የነበረው በተለምዶ ቀዝቃዛ ጦርነት ተብሎ የሚጠራው የርእዮተ ዓለምና የሃያላን ፍጥጫ ነው::

ባለንበት ወቅት በኢትዮጵያ ባለው ፖለቲካዊ መድረክ በመንቀሳቀስ ላይ ካሉት ፓርቲዎች ውስጥ ብዙዎቹ ከአርባ ዓመት በፊት ያልነበሩ ቢሆኑም ያኔ የተንፀባረቁት የፖለቲካ ልዩነቶች እና የተስተናገዱባቸው ስልቶች አሁንም ቢሆን መንፀባረቃቸውና ጫና ማሳረፋቸው አልቀረም::

በመሆኑም አሁን ወደ አለው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች ሁኔታ እና የህብረት ጥያቄ ከመግባታችን በፊት ያኔ የተከሰቱትን ፖለቲካዊ ልዩነቶችና አቋሞች በአጭሩም ቢሆን መዳሰስ የአሁኑን ሁኔታና ችግርን በተሻለ ለመገንዘብ ይረዳል።

**1.1 <u>ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች</u>:-**

በስድሳዎቹ በነበረው የጋለ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ይሁን እሱን ተከትለው ብቅ ባሉት ፖለቲካዊ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ውስጥ በርካታ የፖለቲካዊ ጉዳዮች ተነስተዋል። ያኔ ከተንሸራሸሩት ዋና ዋና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ አንደኛ በብሄር ጥያቄና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ሁለተኛ በርዕዮተ ዓለም ልዩነቶች ምክንያት የተነሱ የፖሊሲ ልዩነቶች፣ ሶስተኛ በመሬት ጥያቄ የነበረው የጦፈ ክርክር ይታወሳሉ።

የአፄውን ስርዓት በመቃወም ይንቀሳቀሱ በነበሩት ፖለቲከኞች አካባቢ መሬት ላራሹ ይሁን በሚለው ጉዳይ ላይ ልዩነት አልነበረም ለማለት ይቻላል፡ ምናልባት (እሱም ምናልባት ነው) ልዩነት ከነበረ የመሬት ባለቤት መንግስት ይሁን ወይስ አራሹ ራሱ ይሁን በሚለው ጉዳይ ዙርያ ነው ። የጎላ ልዩነት የታየው በመሬት ሳይሆን በመጀመሪያዎቹ ሁለት ጉዳዮች ዙሪያ ነበር።

ዘውዳዊው አገዛዝ ከካፒታሊስቱ ርእዮተ ዓለም አቀንቃኝ አለማዊ ኃይሎች ጋር እጅግ የተቆራኘ ስለነበረ እና ለዘውዳዊው አገዛዝ የነበረው ጥላቻ እሱን አቅፍው በያዙት የምዕራብ ኃይሎች ላይም በማነጣጠሩ፤ የካፒታሊስት ርእዩተ ዓለም ከዚህ ጋር ተደርቦ የታየበትና በአማራጭነት ጎልቶ ያልወጣበት ሁኔታ ነው የነበረው።የንጉሱ አገዛዝ ወድቆ ደርግ ስልጣን ከያዘ በኂላም ቢሆን እንደ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረት ያሉ የካፒታሊስት ርእዮተ ዓለምን የሚያቀነቅኑ ተቃዋሚዎች ብቅ ከማለታቸው በስተቀር አብዛኛዎቹ የደርግን አገዛዝ ይቃወሙ የነበሩት ፖለቲካዊ ኃይሎች በርእዬተ ዓለም ደረጃ የማርክስ ሌኒናዊ ርእዬተ ዓለም አቀንቃኞች ነበሩ። በመሀከላቸው የነበረው ልዩነት በማርክስ ሌኒናዊ ርእዬተ ዓለም ክልል ተሁኖ ከኢትዮጵያ ሁኔታ አንጻር እንዴት ተግባራዊ ይሁን በሚል በአተረጎጐም ዙሪያ የተከሰቱ ልዩነቶች ነበሩ።

ደርግን ጨምሮ ደርግን ይቃወሙ የነበሩ ግራ ዘመም ተቃዋሚዎች፤ መሬት ላራሹ ከማለት አልፈው መሬት የመንግስት ይሁን በሚለው ላይም ስምምነት ነበራቸው። ትግሉን መምራት ያለበት ማርክስት ሌኒናዊ ፓርቲ መሆኑ ላይ፣ የሚቋቋመው መንግስት የላብ አደር መንግስት መሆኑ ላይ፣ ኢኮኖሚው በመንግስት ሙሉ ቁጥጥር ስር መዋሉ ላይ፣ የግል ባለሀብት መክሰም ያለበት መደብ መሆኑ ላይ፣

መንግስታዊ ይሁን መንግስታዊ ያልሆኑ አደረጃጀቶች የላብ አደር ፓርቲው አመራር መቀበላቸው የግድ መሆኑ ላይ፣ ወዘተ. ብዙም ልዩነት አልነበራቸውም።

በማርክሲስት ሌኒንስት ርእዮተአለም መሰረት ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች የሚታዩት ከላብ አደሩ ጥቅም አኳያ ስለሆነ ሰብአዊ መብትን ጨምሮ ሃሳብ የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ የመቃወም፣ ወዘተ. . . የመሳሰሉት ዴሞክራስያዊ መብቶች ለሁሉም ሳይሆን ለተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚፈቀዱ ውሎ አድሮም በማርክሲስት ሌኒንስት ፓርቲው በጎ ፈቃድ የሚሰጡ ፓርቲው ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ የሚገደቡ ነበሩ።

በብሄር ጥያቄና በኢትዮጵያ አንድነት ዙሪያ በተከሰተው ልዩነት ላይም የርእዮተ ዓለም ዳራ መኖሩ ባይካድም በዚህ ጉዳይ ዙርያ የተከሰተው ልዩነት ወደ ኢትዮጵያ እውነታና ሁኔታ እጅጉን የተጠጋ እና በዚሁም ተመስርቶ የተከሰተ ልዩነት ነበር ለማለት ይቻላል።

የብሄር ልዩነት እና የብሄር ጭቆና መኖርን የሚቀበል እንደዚያም ሆኖ ግን የብሄር ጥያቄን ማቀንቀን ለኢትዮጵያ አብዮት እንቅፋት አድርጎ የሚመለከት ሀሳብ ባንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የብሄሮችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን የሚቀበል፣በዚህ መርህ በእኩልነት የተመሰረተን አንድነት ከመቀበል አንስቶ እስከ መገንጠልና የተለያዩ መንግስታትን እስከ መፍጠር ድረስ የሚሄድና ለዚህ ብሎ የኢትዮጵያ አንድነት መሰዋእት ሊሆን የሚችል ነገር አድርጎ እስከ ማየት የደረሰ አመለካከት ነበር።

በብሄር ጥያቄ ዙርያ ይሄን ያህል ልዩነት ቢከሰትም ሁለቱም ወገኖች የማርክስ ሌኒናዊ ርእዮተ ዓለም ተከታይ የነበሩ በመሆናቸው በሌሎቹ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ግዙፍ ልዩነት አልነበራቸውም።

## 1.2 ቀዝቃዛው ጦርነት በስድሳዎቹ የኢትዮጵያ ፖለቲካ የነበረው ጫና፦

ቀዝቃዛ ጦርነት ተብሎ በሚጠራው ዘመን ዓለም በሁለት ተፎካካሪ ርእዬቶችና ካምፖች የተከፋፈለችበት፣ በሁለቱም የነበረው የርእዬተ ዓለም እና የፖለቲካል ኢኮኖሚ ልዩነቶች ተከትሎ መንግስታት ካንዱ ወይ ከሌላው ወገን እንዲሰለፉ የሚጠየቁበት፣ ተሰላፊዎችና ተከታዬችን ለማብዛት በሁለቱ ካምፖች መካከል ታላቅ እሽቅድድምና ውድድር የተያዘበት፣ አንዱ የራሱ ስርዓት የተሻለ መሆኑን ለማሳየትና ለመማረክ ከፍተኛ መደለያ መስጠትን ጨምሮ ትልቅ የህዝብ ግንኙነትና የዲፕሎማሲ ስራ የሚሰራበት ወቅት ነበር።

ይህ ዓለም አቀፋዊ ፉክክር ወደ ኢትዮጵያና አካባቢያችንም ዘልቀዋል፡፡በንጉሱ ዘመን የኢትዮጵያ መንግስት ከምእራቡ አለም ጋር የቆመበት የሲያድባሬ መንግሰት ደግሞ ከምስራቁ አለም የቆመበት፣በዚህ ሳብያ በኢትዮጵያ እና በሶማልያ መሃከል ከቆየው ፉክክር በሰተጀርባ የሁለቱ ሃያላን መንግስታት ፉክክርም የታየበት ሁኔታ ተከስቶአል፡፡ወደ ሃገር ውስጥ ሲመጣም ከንጉሱ መንግስት በተፃራሪ የቆሙት ፖለቲከኞች አብዛኛዎቹ ግራ-ዘመም አመለካከት ያራመዱበት ሁኔታ ነበር፡፡

በዘውዳዊው አገዛዝ ላይ ለነበረው ተቃውሞ ማአከሉ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ እንደበረ ይታወቃል፡፡የዚህ እንቅስቃሴ ዋናው ተዋናይ አገር ውስጥ የነበረው ተማሪ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በትምህርት ላይ የነበረው ኢትዮጵያዊም ጠንካራ ህብረት መስርቶ የሚታገልበት ሁኔታ እንደነበር፣በዚህ እንቅስቃሴ ወስጥ በተከሰተ የሃሳብ ልዩነት ምክንያት ደርግ ወደ ስልጣን እንደመጣ ክፍፍሉ የፓርቲ መልክ ይዞ አንዱ ወገን በዋናነት መኢሶን ተብሎ በሚጠራው የፖለቲካ ድርጅት ዙርያ፣ ሌላው ወገን ደግሞ ኢህአፓ በሚባለው የፖለቲካ ድርጅት ዙርያ መሰባሰባቸው ይታወቃል፡፡ሁለቱም ወገኖች በደርግ ባህሪና ምንነት፣ እንዲሁም ከዚሁ በሚመነጩ በርካታ አቋሞች ምክንያት ሲለያዩ ውጭ አገር የነበረው ፍጭት ወደ አገር ውስጥ ዘልቆ በሁለቱ መሀከል ደም መፋሰስ አስከትሏል፡፡

ደርግ ከምዕራቡ ዓለም ወጥቶ ወደ ሶቭየት መራሹ የሶሻሊስት ካምፕ ሲቀላቀል የምዕራቡ ዓለም ደግሞ ሶቭየት ህብረት በአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ ያገኘችውን መቆናጠጫ ማስጣል ከሚል የኢትዮጵያ አጎራባች ሃገራት ደርግን እንዲተናኮሉ፣ድርግን የሚቃወሙትን ሃይሎች እንዲያስጠልሉና እንዲረዱ ሲያበረታታ ቆይቷል፡፡በአጠቃላይ የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን በተለያየ መልኩ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ገፀ-ምድር ላይ የራሱን አሻራ ትቶኣል፡፡

## 1.3 ፖለቲከኞች ልዩነቶቻቸው ለመፍታት የተከተሏቸው ስልቶች፡-

የፖለቲካ ልዩነቶቹ እንዳሉ ሆነው የዛኔው ዘመን ፖለቲከኞች ልዩነቶቹን ለመፍታት የተጠቀሙባቸው ስልቶች፤ ልዩነቶቹን ይበልጥ በማወሳሰብ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በአጼ ኃ/ስላሴ ይሁን በደርግ ዘመን ሀሳቦችን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመግለፅና ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ ለማቀራረብና ለማስተናገድ የሚያስችል ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ አልነበረም፡፡ በሃገር ወቅታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች ዙሪያ በግልፅ ለመወያየትና ሃሳቦችን ለማንሸራሸር ቢሞከር ከስርአቱ የሚሰጠው መልስ ዱላና አረር

ነበር፡፡ እነርሱን የሚቃወሙት ፖለቲከኞች ሳይቀሩ በመሃከላቸው የተከሰተውን የሃሳብ ልዩነት ለመፍታት የተጠቀሙበት ዘዴ የኃይልና የቃታ መሳሳብ ዘዴ ነው፡፡

ያኔ ፖለቲከኞቹ ይመሩበት የነበረው ማርክስ ሌኒናዊ ርእዩተ ዓለምም ለዚሁ ችግር የራሱ አሉታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡

ማርክስ ሌኒናዊ ፍልስፍና ሕብረተሰብ ተፃራሪ ጥቅም ባላቸው መደቦች እንደሚቆምና የህብረተሰቡ እድገት በዚህኛው ቅራኔ ምህዋር እንደሚሽከረከር፣ በእንደዚህ ዓይነት ተፃራሪ ጥቅም ላይ የተመሰረቱ ቅራኔዎች የሚፈቱበት ዘዴ ኃይልና ኃይል ብቻ እንደሆነ  ያስቀምጣል፡፡ የዚህ ርእዮተአለም ተከታይ ፖለቲከኞች በመሃከላቸው ልዩነት ሲከሰት ልዩነቱን ሊታረቅ አይቻልም ከሚባለው የመደብ ቅራኔ ጋር እያያያዙ አንዱ ሌላውን የማጥፋት አካሄድ ይከተላሉ፡፡ በስድሳዎቹ የነበሩት ፖለቲከኞች በመሀከላቸው ልዩነት በተነሳ ቁጥር ልዩነቱ የሚፈቱት አንዱ ሌላውን በማጥፋት እና በመግደል እንዲሆን በማድረጉ ረገድ ይህ አስተሳሰብ ትልቅ ጫና ነበረው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ አይነቱ  እርምጃ በተካረረ የፖለቲካ ትንተናና ፕሮፖጋንዳ ታጅቦ ነበር የሚፈፀመው፡፡

ይህ መጥፎ የግንኙነት አፈታት ታሪካችን ከአስርት ዓመታት በኋላም ከሰው ስነ ልቦናና አሁን ካሉት የፖለቲካ ልዩነቶች ጨርሶ ሊጠፋ አልቻለም፡፡ ወደፊትም ይህ የታሪክ ዳራ ፖለቲካ ልዩነቶችን በማጥበብ እና ህብረትን በመፍጠሩ ሂደት ላይ ሳንካ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 2. <u>የስድሳዎቹ ፖለቲካ የወለዳቸው የአደረጃጀት መልኮች</u>፡-

የስድሳዎቹ ፖለቲካ ራሱን የገለፀበት የአደረጃጀት መልክም ነበረው፡፡ የዚያን ዘመን አደረጃጀት በአንድ መልኩ የጋራ ሊባል የሚችል አጠቃላይ ባህርይ ሲኖረው በብሄር ጥያቄ ዙሪያ ከነበረው ልዩነት በተያያዘ መልኩ ለየት ያለ ገፅታም ነበረው፡፡

### 2.1 <u>አጠቃላይ ባህሪው</u>፡-

ማርክስሌኒናዊ ርእዩተ ዓለም ብቸኛ እና የአንድ ፓርቲ አመራር መርህን ነው የሚከተለው፡፡ የወዝ አደር ጥቅም ወጥ ነው፣ ይህንን ጥቅም ሊያሳካ የሚችለው አንድ የወዝ አደር ፓርቲ ብቻ ነው ይላል፡፡ ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥቅሞች መካከል ከወዛደር ጥቅም ጋር ሊሄዱ የሚችሉት ይጠበቃሉ፣ የገዢ መደቦች ጥቅም ግን አይጠበቅም፣ ላይጠበቁ ደግሞ አደረጃጀት እንዲኖራቸውም አይፈቀድላቸውም፡፡ በዚህ ምክንያት በማንኛውም መልኩ የሌሎች ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ህልውና አይቀበልም፡፡

ማርክስሌኒናዊ ርእዩተ ዓለም ከወዝ አደር ፓርቲ በመለስ ሌላ ፓርቲ ባይቀበልም ሌሎች የህዝብ አደረጃጀቶች መኖራቸውን ይቀበላል:: ሰራተኞች የሰራተኛ ማህበር እንዲያቋቁሙ፣ ሴቶችም የሴቶች ማህበር እንዲያቀቁሙ ይፈቀዳል:: እነዚህ የሚደራጁት ግን በሶሻሊስት አብዬት ተጠቃሚዎች በመሆናቸው ለሶሻሊስት አብዬት ድጋፍ እንዲሰጡ ከሚል ነው:: የወዝ አደር ፓርቲውን ፕሮግራም ማሳካት እግረ መንገዱም የእነዚህም የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም ዳር ማድረስና ማሳካት ስለሆነ ለዚሁ ስኬት ተብሎ የሰራተኛው ማህበርም የሴቶች ማህበርም ሌሎችም በወዝአደር ፓርቲው ስር የመውደቅ ግዴታ ይጣልባቸዋል::

ሰራተኞቹ የራሳችንን ጥቅም ለማስከበር ራሳችንና ነፃነታችንን ጠብቀን እንታገላለን ቢሉ እና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እንቅስቃሴ ቢያደርጉ ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ይሆናል ምትም ሊያስከትል ይችላል:: እነዚህ አደረጃጀቶች የሚፈለጉት ግንባር ቀደም እና ብቸኛ መሪ ነኝ የሚለውን ፓርቲ ፕሮግራም አስርፀው የአባሎቻቸው ድጋፍ ሊያስገኙ ካልሆነ በስተቀር የአባሎቻቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለማስከበር አይደለም:: እንደዛም እንዲሆኑ አይፈለግም አይፈቀድላቸውም::

ይህ አመለካከት በሁሉም ግራ ዘመም ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶች የሚታመንበት መርህ ስለሆነ ብሄራዊም ሆኑ ሕብረብሄራዊ ሁሉም ድርጅቶች ተግባራዊ ሲያደርጉት ታይቷል::

**2.2 <u>የብሄር እና ሕብረብሄር አደረጃጀቶች</u>:-**

የማርክስሌኒንስት ርእዩተ ዓለም አራማጅ ድርጅቶች የሚጋሩት የአደረጃጀት መርህ ቢኖርም በብሄር ጥያቄ ዙሪያ ካለው ልዩነት በተያያዘ ሁለት የአደረጃጀት ሞዴሎች ተስተውሎባቸዋል::

እነሱም:-

ሀ. የሕብረብሄር የአደረጃጀት ሞዴል

ለ. የብሄር የአደረጃጀት ሞዴል ናቸው::

**2.2..1 <u>ሕብረ ብሄራዊ የአደረጃጀት ሞዴል</u>:-**

ይህ የአደረጃጀት ሞዴል የኢትዮጵያ የሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ተወላጅ ፖለቲከኞች እንደ ግለሰብ የተቀላቀሉበት ወጥ አደረጃጀት ነው:: በዚህ አደረጃጀት የብሄር ብሄረሰብ ልዩነት ቢኖርም ሁሉም እንደ አንድ ሀገር ዜጎች በአንድ ሕብረ ብሄራዊ ድርጅት ውስጥ መታቀፍ አለባቸው ይላል:: እንደዚህ ያለው አደረጃጀት በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች መዋቅር ሲዘረጋ ይህንን መርህ የተከተለ ስለሚሆን በዛ አካባቢ ያሉትን ፓርቲውን ለመቀላቀል ፍቃደኛ የሆኑትን ዜጎች በሙሉ ያቅፋል::

ይሄን የአደረጃጀት ሞዴል የሚከተሉት ወገኖች በአቋም ደረጃ የብሄር ብሄረሰብ መብት መከበር አለበት የሚሉ ሊሆኑ ይችላሉ፤ይህም ሆኖ የሁሉም ብሄረሰብና ብሄረሰብ ተወላጆችን ያቀፈ ሕብረ ብሄራዊ ፓርቲ እስካለ ድረስ በሱ አማካኝነት የብሄር ብሄረሰብ መብትን ማስከበር ይቻላል ይላሉ::

ማርክሲስት ፓርቲ ነን የሚሉት በተለይ በኢትዮጵያ የብሄር ጭቆና እንዳለና ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸው እድል በራሳቸው የመወሰን መብት እንዳላቸው በመርህ ደረጃ ቢቀበሉም የወዛደር ጥቅም የመደብ ጥቅም በመሆኑ ብሄር፣ ቀለምና ሃይማኖት አይልም፤ የአንድ መደብ ጥቅም ለዛ ጥቅም በሚቆም አንድ ሀገር አቀፍ ፓርቲ አመራር ስር መውደቅ አለበት ይላሉ:: ከዚህም በመነሳት የብሄር አደረጃጀት የወዝ አደሩን አንድነት የሚከፋፍል ጠባብ እና ፀረ ላብአደር አመለካከት ነው ይላሉ::ለዚሁ በህወሓትና በኢህአፓ መካከል የነበረው ልዩነት በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል ::

ይህ ሞዴል በሊህቃንና በከተሜው ውስጥ ቀላል ያልሆነ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ከተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች የተውጣጡ የሀገሪቱ ሊህቃንና ከተሜዎች በዚህ የሚታቀፉበት ሁኔታ ይታያል:: ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሲኬድ በአማራ ክልል እና ቅልቅል የሆነ አኗኗር ባላቸው አካባቢዎች ለመዝለቅ ቢችልም የአንድ ብሄር ብሄረሰብ ተወላጆች በመደዳ በሰፈሩባቸው አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ገጠሮች በስፋት ሊዘልቅ ያልቻለበት ሁኔታ ይታያል::

**2.2..2** <u>**የብሄር አደረጃጀት ሞዴል**</u>**:-**

የብሄር አደረጃጀት ሞዴል ከአንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ የተወለዱ ዜጎችን በግለሰብ ደረጃ በአባልነት ያቀፈ አደረጃጀት ነው:: የዚህ አደረጃጀት ደጋፊዎች በኢትዮጵያ የብሄር ጭቆና አለ፣ በኢትዮጵያ የብሄሮች ጭቆናን ማስወገድ፣ የብሄሮች እኩልነት ማረጋገጥ፣ የብሄሮች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ማረጋገጥ ከዛም ብሄሮች ከፈለጉ ተገንጥለውም የራሳቸውን ነፃ መንግስት እንዲያቋቁሙ ማድረግ አንድ ራሱ የቻለ የዴሞክራሲ ጥያቄ ስለሆነ ይህንን ማስከበር ይገባል:: ይህን ማስከበሪያ አንዱ መሳሪያ ድርጅት እንደመሆኑ ለብሄር መብት ሲታገሉ በብሄር ተደራጅቶ መቆሙ ለዛ ብሄር መብት ማስጠበቅያ መሳሪያ እንደሰጡት ይቆጠራል ብለው ስለሚያምኑ በብሄር መደራጀትን ያራምዳሉ::

በብሄር የተደራጁ ዜጎች አላማቸው የተለያየ ሊሆን ይችላል:: የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚለው መርህ ራስን በራስ በማስተዳደር መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን የሚሹና አጠቃላይ በሀገራዊ ማዕቀፉም የብሄር በሄረሰብ እኩልነት ባረጋገጠ መልኩ እንዲዋቀር የሚፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ፣ለመገንጠልም ለአንደነትም ቁርጥ ያለ አቋም ያልያዙ ነገሩ በህዝብ ውሳኔ ይቋጭ የሚሉ ሊሆኑም ይችላሉ፣ ወይም ደግሞ ተለይቶ የራስን መንግስት ሚቋቋም እንደ አላማ የያዙ ሊሆኑ ይችላሉ::የመጨረሻ ግባቸው ይሄን ያህል

የተለያየና የተራራቀ ሊሆን ቢችልም ሁሉም አንድ የሚያደርጋቸው ግን የብሄርና የብሄረሰባቸው መብት ከማስከበር አኳያ በብሄር መደራጀትን እንደ አንድ አስፈላጊ አደረጃጀትና እንደ አንድ አስፈላጊ መሳሪያ የሚያዩ መሆናቸው ነው::

ይህ አደረጃጀት አሁንም ድረስ ሕብረ ብሄራዊ በሆነችው አገራችን በተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች አካባቢ እየታየ ያለ የአደረጃጀት መልክ ነው፣ የሚመለከተው ብሄር ልሂቃን ይሳተፉብታል:: በሚመለከተው ብሄር አካባቢ አሰፋፈርን ተከትሎ እስከ ጫፍ ድረስ የመዝለቅ ችሎታ ያለው በመሆኑ የየብሄር ብሄረሰቡ ልሂቃንን ቀላል በማይባል መልኩ ከማሳተፉ ባሻገር በገጠር የሚኖረውን የዛ ብሄር ተወላጅ በሰፊው ያሳትፋል::

ይህም ሆኖ የተለያዩ ብሄር ተወላጆች ተሰባጥረው በሚኖሩበት አካባቢ የአንድን ብሄር ተወላጅ ብቻ እየመለመሉ ሌላው የመተው ባህሪ ስላለው ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ ያለመሆን ችግር አለው:: በጋራ የሚኖሩ የጋራ ብሶት ያለባቸውን ዜጎች በጋራ ለማታገል አስቸጋሪነት ስላለው በከተሞችና ተቀላቅለው በሚኖሩ ዜጎች አከባቢ፣ የዚህ ብሄር ተወላጅ ነኝ ብለው ሊፈርጁ በማይፈልጉና በሚቸገሩ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ይሄ አደረጃጀት ተደራሽ ያለመሆን ችግር አለበት::

## **2.3 <u>የሁለቱ ሞዴሎች ንፅፅር</u>:-**

በሞዴልነት የተወሰዱት ሁለቱ ጫፎች ብቻ ናቸው:: በሁለቱም መሀከል የሁለቱንም ባህሪ የወረሰ አደረጃጀት በኢትዮጵያ ፖለቲካ የለም አይኖርም ለማለት አይደለም:: የተያዘውን ጉዳይ በግልፅ ለማሳየት እንዲቻል ነው ሁለቱን ጫፍ የሚመለከቱትን ሞዴሎችን መውሰድ የተመረጠው::

ሁለቱም ሞዴሎች የየራሳቸው ደካማና ጠንካራ ጎራ አላቸው::ሁለት መለኪያዎች ብቻ ላይ በመመርኮዝ ማነፃፀሩ ይሻላል::

1ኛ ከመርህ እና አቋም አኳያ

2ኛ ብዙ ህዝብ ከማሳተፍና ከማቀፍ አኳያ::

ከመርህ አኳያ  ሕብረ-ብሄራዊው ሞዴል ኢትዮጵያን እንደ አንድ ማህበረሰብ እና እንደ አንድ ሀገር ይወስዳል:: ይሄን መነሻ በማድረግ በዚህ ዙሪያ ያሉትን መርሆዎችና አቋሞች ያጠናክራል:: ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ስለ ኢትዮጵያ ዳር ድንበር ወዘተ. የመሳሰሉት የጋራ መርሆዎችንና አቋሞችን ያጠናክራል:: የጋራ የሆነውን የኢትዮጲያዊነት ንቃተህሊናን ይጠብቃል ያጠናክራል:: ይህ ጠንካራ ጎኑ ሆኖ ድክመትም አለው::

ኢትዮጵያዊነታችን ከሕብረብሄራዊነታችን ጋር ያለውን ተፈጥሮአዊ ቁርኝት በሚመለከት ተገቢው ግንዛቤ የለውም::በእኛ አገር ሁኔታ ኢትዮጵያዊ መሆን ሲዳማ፣ትግራዋይ፣አማራ፣ኦሮሞ ወዘተ መሆንም እንደሆነ ያለመገንዘብ፤ ይባስ ብሎ

ደግሞ ኦሮሞነትን ወይም ትግራዋይነትን እንደ ያልኢትዮጵያውነት የማንበብ ሁኔታ ይታይበታል፡፡ ኢትዮያዊነት የብሄር ጭቆና ስጋትን ከማስወገድና እኩልነት ተረጋግጦ ከማየት ምኞች ጋር ያለውን ተፈጥሮአዊ ቁርኝት አይገነዘብም፡፡በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ስፍራ ይዞ የቆየውን የብሄር ጭቆና ተወግዶ የኢትዮጵያ አንድነት በማይናጋ መሰረት ቆሞ እንዲቀጥል የሚሹ ወገኖችን ስጋት ከማሳነስ እና ከማጥላላት ጀምሮ የሚገባውን ክብደትና ትኩረት ይነፍገዋል፡፡በመሆኑም በበርካታ የሃገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ዘንድ በስጋትና በጥርጣሬ የመታየት ችግር ያጋጥመዋል፡፡

የብሄር ሞዴሉ ጋር ስንመጣ የብሄር አደረጃጀትን እንደ የብሄር መብት ማስከበሪያና የብሄር ጭቆናን መከላከያና መግቺያ አስፈላጊ መሳሪያ የሚወስድ መሆኑ አንዱ ጥንካሬው ነው፡፡ ኢትዮጵያ አንድነት ዙሪያ ተሁኖም የብሄር መብት አስፈላጊው ጥበቃ እና ዋስትና እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ በእኩልነትና በመተማመን ላይ ለተመሰረተ፣ የብሄር አድልዎና ጭቆና አደጋና ስጋት የማይኖረው አንድነት በማረጋገጥ ረገድ ፋይዳ ያለው አደረጃጀት ያደርገዋል፡፡

ይህም ሆኖ አደረጃጀቱ ከመርህ አኳያ የራሱ ችግሮችም አሉት፡፡ በብሄር ብሄረሰቦች አደረጃጀት መሀከል መተባበር ተፈጥሮ አገራዊ የሆኑት ጉዳዩች ትኩረት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ግምት ውስጥ የሚያስገባ ቢሆንም ይሄ ግምት ከመሆኑ አልፎ ከፍተት ሆኖ እንዳይቀር አስተማማኝ የሆነ ማስወገጃ ዘዴ የለውም፡፡ ሁሉም የብሄሩን ብቻ እያየ የጋራ የሆኑትን እንደ ኢትዮጵያዊነት፡ ነፃነት፡ ሉአላዊነት ወዘተ. የመሳሰሉት የጋራ እሴቶችና ንቃቶችን ያለባለቤት የማስቀረት አደጋ አለው፡፡ ሁሉም ወደ ራሱ እየጎተተ በህዝቦች መሀከል ሊኖር የሚገባውን የአብሮነት እና የመተሳሰብ ግንኙነትን በአሉታ የመንካት አደጋም ሊኖረው ይችላል፡፡

ከአሳታፊነት አኳያ ሲታይ አብዛኛው ህዝባችን በገጠር የሚኖር ከመሆኑ፣ አብዛኛ ዎቹ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች የታወቀ የየራሳቸው ሊባል የሚችል አሰፋፈር ያላቸው ከመሆናቸው አኳያ በእንደዚህ ያለ ሕብረተሰብ ዘልቆ ለመግባትና ህዝቡን ለመድረስ የብሄር አደረጃጀቱ የበለጠ ተደራሽነት አለው፡፡ በአከባቢው ቋንቋ የሚሰሩ በመሆናቸው የህዝቡን ስሜት የህዝቡን ባህል መሰረት ያደረገ አቀራረብና ስራ በመስራት ረገድ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

በዚህ ረገድም ቢሆን ግን ይህ ሞዴል ድክመቶች አሉት፡፡ እንደ ከተሞች እና እጅግ በተሰበጣጠረ ሁኔታ በሚኖሩ ዜጎች መሀከል በቋንቋና በብሄር ለይቶ ለማደራጀት በዜጎች መሀከል ያለው አንድነትና አብሮ በመታገል ሊገኝ የሚችሉን ውጤት ይቀንሰዋል፡፡ በእንደዚህ ያለ አደረጃጀት አንታቀፍም ያሉና ለትግሉ እና ለሀገር ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ወገኖችንም ያለ ድርጅት ያለ ትግል ተሳትፎ ሊያስቀራቸውና ሊያገላቸው ይችላል፡፡ ከዚህ በተያያዘ ለመደራጀት ያልፈለጉ/ያልቻሉ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች

ባለመደራጀታቸው ምክንያት ከጨዋታው ውጭ ሆነው የእነሱን ጉዳይ የሚመለከት ባለቤት እንዲያጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 3. የደርግ መውደቅና የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ማክተም፡-

ቀዝቃዛው ጦርነት ያበቃበትና ደርግ ከስልጣን የተወገደበት ወቅቶች የተቀራረቡ ናቸው፡፡ ለቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም አመላካች የሆኑ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገቶች ቀደም ብለው እየተጠራቀሙ የመጡ ቢሆኑም የሶቭየት መፍረስና የግንቡ መፍረስ የማክተሚያው ማሳረጊያዎች ነበሩ፡፡ የደርግ ስርዓት ከርእዬተ ዓለም እና ከፖለቲካ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎቹ አኳያ ከሶቭየት ሕብረት መራሹ ካምፕ ጋር እጅግ የተሳሰረ ስለነበረ የዚህ ካምፕ መዳከም ኋላም መፍረስ የደርግን ውድቀት አቅርቦታል፡፡ የሶቭየት ህብረት ድጋፍ እንደተለመደው የማይቀጥል መሆኑ ሲታይና እያቋረጠ ሲሄድ ደርግ ገብቶ የነበረበቱ የጦርነት ማጥ ሊያስቀጥል የማይችልበት ሁኔታ መፈጠር ጀምሮ ስለነበረ የሶቭየት ሕብረት መፍረስን ተከትሎ ደርግም መፍረስ የሚችልበት አለማዊ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በተጓዳኝ ኢህአዴግ መራሹ የትጥቅ ትግል እየተጠናከረ መጥቶ ወደ ድል የተቃረበበት ሁኔታ ስለነበር በ1983 ዓ.ም ላይ የደርግ ማብቂያ ሆነ የኢህአዴግ ዘመንም ተጀመረ ሊባል ይቻላል፡፡

ሁለቱም ክስተቶች በአለም በጠቅላላም፣ በኢትዮጵያም የነበረውን ሁኔታ ቀይረውታል፡፡ አሁን ከያዝነው አጀንዳ የተከሰቱትን ለውጦች በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

### 3.1 አለማቀፋዊው የርእዮተ ዓለም ሽግሽግ፡-

የሶቭየትንና የግንቡን መፍረስ ተከትሎ ማርክሰሌኒናዊ ርእዬተዓለም አፈግፍገዋል፡፡ ሶሻሊዝምን እንገነባለን የሚሉት ፓርቲዎችም የተዳከሙበት እሱ ግድ የሚለው ፖለቲካል ኢኮኖሚ እንደ አማራጭ ለሕብረተሰቡ ከማቀረብ ገሸሽ የተባለበት ወቅት ነው የመጣው፡፡ ይህ ሲባል ርእዬተዓለሙ ጠፍቷል ማለት አይደለም ርእዬተ ዓለሙና እሱ ግድ የሚለውን ፖለቲካል ኢኮኖሚ አስፈላጊ ነው የሚሉ ኃይሎች የሚሉ የሉም ማለትም አይደለም፡፡ በቀዝቃዛው ጦርነት በነበሩበት ደረጃ ግን የሉም ነው ማለት የሚቻለው፡፡

በአሁኑ ወቅት ካፒታሊስት ርእዬተ ዓለም የበላይነት አግኝተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ሲያቀነቅኑ የነበሩ ወገኖችም አማራጭ ፓርቲ

ስለማስተናገድና ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት ራስን ክፍት ወደ ማድረግ ሄዱ:: ፖለቲካ ያለ ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የማይታሰብ የሆነበት ስልጣን ያለ ምርጫ መያዝ የሚወገዝበት ወቅት መጣ::

በኢኮኖሚም እንደዚሁ መንግስት ሁሉንም የሚቆጣጠርበት ራሱ አስተዳዳሪ ራሱም ባለሀብት የሚሆንበት መንገድ ተቀባይነት እያጣ፣ በዚሁ ፈንታ መንግስት የኢኮኖሚ ይዞታውን ለባለሀብቶች እየለቀቀ ሁኔታዎችን ለነፃ ገበያ የሚያመቻችበት መንገድ እንዲከፈት የሚጠይቁ የተለያዩ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች መቀስቀስ ተጀመሩ:: ይህንን ከማስፈፀም አኳያም የአለም ባንክና የአለም የገንዘብ ድርጅት በዋና አስፈፃሚነት እየተንቀሳቀሱ እነዚህ የኢኮኖሚ ለውጦችን መቀበል ለእርዳታና ለኢኮኖሚ ድጋፍ እንደ ቅድመ ሁኔታ እያስገቡ ይሄ አቅጣጫ በአለም ደረጃ እንዲናኝ በስፋት ተንቀሳቀሱ::

የሰበአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ሰፊ ተቀባይነት ከማግኘታቸው ጎን ለጎን የብሄሮች እና የአናሳ ህብረተሰብ ክፍሎች መብት የመከበር ጥያቄ እንደዚሁ ተሰሚነትና ተደማጭነት እያገኙ መጡ::

### 3.2 ይህን ተከትሎ በኢትዮጵያ የተከሰቱ ለውጦች:-

በኢትዮጵያ የተከሰቱትት ለውጦች በሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል

### ሀ. የኢትዮጵያው የርእዮተ ዓለም ሽግሽግ:-

የአለም አቀፍ ሁኔታውን ተከትሎ በኢተዮጵያ ፖለቲከኞቹም ዙሪያ የርእዬተ ዓለም ሽግሽግ መከሰቱ አልቀረም:: ደርግ ራሱም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታው እየተቀየረ ሲሄድ ቅይጥ ኢኮኖሚ የሚባል ነገር አንቀሳቅሶ ነበር:: ህወሐት የብሄር ድርጅት ቢሆንም ማርክሲስት ሌኒንስት ርእዬተ ዓለምን ያቀነቅን ነበር:: ህወሐትን የሚመራ ማርክሲስት ሌኒንስት ሊግ ትግራይ (ማሌሊት) የሚባል ፓርቲ በህወሐት ውስጥ ተመስርቶ ይንቀሳቀስ ነበር:: ይህ ፓርቲ ህወሐትን በበላይነት የሚመራ የራሱ መዋቅርና ፕሮግራም የነበረው ፓርቲ ነው:: በይዘቱ ላይ ልዩነት ቢኖረውም ብዙ እየተነገረለት ያለው አብዬታዊ ዴሞክራሲ ወደ ሶሻሊዝም መዳረሻ እንዲሆን ተብሎ የተቀረጸ የዚህ ፓርቲ ዝቅተኛ ፕሮግራም ነበር::ኢህአዴግ እንደተመሰረተም እንደዚሁ በውስጡ ማርከሰሌኒናዊ ፓርቲ ነበረው:: እንደህወሃት ሁሉ ኢህአዴግም አብዬታዊ ዴሞክራሲን እና ሶሻሊዝምን ከላይ በተገለፀው መልኩ ነበር አቆራኝቶ የሚያያቸው::

የሶቭየት ሕብረት መፈረካከስ ሲመጣ ህወሐትና ኢህአዴግም የርእዬተ ዓለም ማፈግፈግ አድርገዋል:: በአንደኛው የኢህአዴግ ጉባኤ ከዛ በፊት ይቀነቀኑ የነበሩ አቋሞች ለዘብ ብለው ስለ የግለሰብ መብት፣ ስለ ዴሞክራሲያዊ መብት፣ ስለ መድብለ ፓርቲ፣ ስለ የግል ባለሃብት ሚና በኢኮኖሚ፣ የመሳሰሉት ነገሮች በአዲሱ ፕሮግራም

ቦታ እንዲያገኙ ተደረገ። ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባም ይህንን ነው ተግባራዊ ማድረግ የጀመረው።

በጦርነት የደቀቀ ኢኮኖሚ ነበርና ይህ ኢኮኖሚ ያገግም ዘንድ የውጭ ድጋፍ አስፈላጊ ነበር። የውጭ ድጋፍ ይገኝ ዘንድ በአለም ዓቀፍ ደረጃ ሲገፋበት የነበረ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ እንዲደረግ የአለም የገንዘብ ተቋም (IMF) እና የአለም ባንክ ገፍተው የሚሰሩበት ሁኔታ ስለ ነበር ኢህአዴግ በዚህም ሳቢያ ቀስ በቀስ እያፈገፈገና አቋሞቹ ላይ ሽግሽግ እያካሄደ መጥቷል።

በፖለቲካ እና በርእዮተ ዓለም የተደረገው ሽግሽግን ኢህአዴግን የሚመለከት ብቻ አልነበረም። በስድሳዎቹ እና በሰባዎቹ የማርክሲስት ርእዮተ ዓለም አንግበው ሲታገሉ የነበሩት እንደ መኢሶን እና ኢህአፓ የመሳሰሉ ነባር ፓርቲዎችም በዚሁ ዙሪያ የአቋም ሽግሽግ አሳይተዋል።

<u>ለ. ሰላማዊ ፖለቲካ ትግል ህጋዊ እውቅና ስለማግኘቱ:-</u>

ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ እንደመጣ ሌሎች ፓርቲዎችንም ያሳተፈ የሽግግር መንግስት ምስረታ ፕሮግራም ነበር ይፋ ያደረገው። በዚህ መሰረት ደርግን ሲቃወሙ የነበሩ የታጠቁ ድርጅቶች እና ያኔ ብቅ ብቅ ያሉት አዳዲስ ድርጅቶች ከኢህአዴግ ጋራ የሽግግር መንግስት ሲመሰርቱ በዋናነት ውጭ አገር ሲንቀሳቀሱ የነበሩት እንደነ መኢሶንና ኢህአፓ ዓይነቶቹ ነባር የፖለቲካ ድረጅቶች ግን በዚህ ሳይሳተፉ ቀሩ።

በአጠቃላይ በሰላማዊ መንገድ የራስን ፖለቲካዊ እምነቶችና አቋሞች ማራመድ እውቅና አግኝቶ በዚህ መሰረት ፓርቲዎች መንቀሳቀስ የጀመሩበት ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ይቻላል።

ይሄም ሆኖ ሁሉም ወደ ሰላማዊው የትግል መድረክ ገብተዋል ማለት አይደለም የሽግግር መንግስቱን በመመስረት ላይ ተሳታፊ የነበረው ኦነግ በኋላ ላይ ከሽግግር መንግስቱ ወጥቶ ወደ ተቃዋሚ ጎራ ከመቀላቀል ባሻገር ወደ ድሮው የትጥቅ ትግሉ ተመልሶ አሁንም ትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛል። የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ንቅናቄ በሽግግሩ ጊዜ ወደ ሰላማዊ ትግል የመመለስ አዝማሚያ አሳይቶ የነበረ ቢሆንም ብዙም ሳይቆይ ወደ ትጥቅ ትግሉተመልሷል። ከዚህ አልፎ በቀጥታ በትጥቅ ትግል ተሳታፊ ባይሆኑም ከኢትዮጵያ ውጭ ሆነው በተቃዋሚ ደረጃ ሊፈረጁ የሚችሉ ፖለቲከኞች በአውሮጳና በአሜሪካ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ አለ። ዲያስፖራው አብዛኛው ባለበት ሆኖ ኢህአዴግን የሚቃወምበት ሁኔታ ነው ያለው።

ሰላማዊ የትግል መልክ ህጋዊ እውቅና ቢያገኝም በተለያዩ ምክንያቶች አሁንም አገር ውስጥ ገብተው ሰላማዊ ትግል ለማስቀጠል ያልቻሉ ከዛም አልፎ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ያሉ ፖለቲካዊ ኃይሎችና ድረጅቶች እንዳሉ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል።

<u>ሐ. የብሄር ብሄረሰብ ጥያቄ እውቅና ማግኘቱ:-</u>

ኢህአዴግ በስልጣን ከመጣ ወዲህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እውቅና ያገኘውና ደምቆ የወጣው ፖለቲካ ጉዳይ ቢኖር የብሄር ብሄረሰብ መብት ነው:: ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦች አገር እንደሆነች በኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰብ ጭቆናና አድልዎ እንደቆየ ይህ መታረም እንዳለበትና ሁሉም ብሄረሰቦች በእኩልነት የሚኖሩባት ስርዓት መገንባት እንደሚገባ ግንዛቤ ተወስዶበታል:: መጀመሪያ ላይ ቻርተሩ ቀየት ብሎም ህገ መንግስቱ ይህን ግምት ባስገባ መልኩ ተቀርጿል:: በዚህም መሰረት ብሄር ብሄረሰቦች በተለያየ ደረጃ የራሳቸው ውስጣዊ አስተዳደር ያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሮአል::

በኢትዮጵያ ፖለቲካ የታየው ትልቁ ለውጥ ይሄ ሆኖ በዚህ ዙሪያ አሁንም ድረስ ያልረገቡ በርካታ ሃሳቦችና ልዩነቶች በመሃከላችን ተንፀባርቀዋል:: ህገ መንግስቱ የብሄረሰቦች መብት እስከ መገንጠል ድረስ በሚሄድ መልኩ በመደንገጉ ይሄን በሚደግፉና ይሄን በሚቃወሙ ወገኖች መሃከል ልዩነት አለ::

በመንግስት አወቃቀር ረገድም ብሄር ብሄረሰብን መሰረት ያደረገ ፌደራላዊ አወቃቀር መኖሩ ላይም ልዩነት አለ:: የብሄር ጥያቄ እውቅና ማግኘቱ የአንድነት ጥያቄን እና የጋራ የሆኑትን ነገሮች እንዲገፉ አድርገዋል፣ መሳሳብና አላስፈላጊ ግጭቶች ለመፈጠራቸው ምክንያት ሆኖአል የሚሉ ወገኖች በአንድ ወገን ሲኖሩ በሌላ በኩል ደግሞ ይሄ መብት መከበር እንዳለበት ተቀብለው፣ እየታየ ያለው መሳሳብ ከብሄር መብት መከበር ጋር ተያይዞ እንደችግር መታየቱን ትክክለኛ እንዳልሆነ የሚያስቀምጡም አሉ::

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ለውጥ ከተከሰተ ወዲህ ከዛ በፊት ባልታየ መልኩ የብሄር ጥያቄ እውቅና ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን ደምቆና ጎልቶ መውጣቱ ከዚህ ጋር በተያያዘም በርካታ የፖለቲካ ልዩነቶች እየተፈጠሩ መጥተዋል::

**3.3 በአደረጃጀት በኩል የታዩ ለውጦች፡-**

ከፍብለን ያየናቸው ሁለት የአደረጃጀት ሞዴሎች ግለሰቦችን ነው በአባልነት የሚይዙት:: ብሄራዊ ድርጅት የአንድ ብሄር ተወላጆችን በአባልነት ሲያቅፍ ሕብረ ብሄራዊ ድርጅትም የተለያዩ ብሄር ብሄረሰብ ተወላጆችን በግለሰብ ደረጃ ይይዛል:: እነዚህ እንዳሉ ሆነው በሂደት ለየት ያሉ አደረጃጀቶች ተከስተዋል::

አንድ እንደ ለየት ያለ አደረጃጀት ሊወስድ የሚችለው የኢህአዴግ አደረጃጀት ነው:: ኢህአዴግ በአንድ ወቅት ብሄራዊ ድርጅቶችንና ሕብረ ብሄራዊ ድርጅቶችን አቅፎ ይዞ ነበር:: አሁን ብአዴን ተብሎ ያለው ድርጅት ኢህዴን የሚባልና ይዘቱም ሕብረ ብሄራዊ የሆነ ድርጅት ነበር:: በሂደት ኢህዴንም ብኣዴን ሆነ፣ ደቡብ ላይ ግን ዴሂዴን የሚባል ህብረብሄራዊ ግን ክልላዊ የሆነውና ብሄራዊው የኦሮሞ ድርጅት ኦህዴድን የያዘው አንድ

ግንባር ፈጠሩ፡፡ይህ እውነታ የኢህአዴግ አደረጃጀትን ከግለሰቦች ባሻገር ድርጅቶችን በአባልነት ያቀፈ የፓርቲ አደረጃጀት እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ሌላው የአደረጃጀት ለውጥም በኢህአዴግ ሰፈር የታየ ሆኖ አባል እና አጋር የሚባሉ ድርጅቶችን መፍጠሩ ነው፡፡ አባሎች የሚባሉት አራቱ ድርጅቶች ሲሆኑ አጋር የሚበሉት ድርጅቶች ደግሞ ከአራቱ ክልሎች ውጪ የሚንቀሳቀሱት የክልል ድርጅቶች ናቸው፡፡አጋሮቹ ኢህአዴግን በሙሉ አባልነት እንዲቀላቀሉ አልተፈለገም ሆኖም ግን ሁለተኛ ደረጃ አሰላለፍ ተፈጥሮ አጋር በሚል ማዕቀፍ እንዲጠቃለሉ ተደርጎአል፡፡

በተፎካካሪ ድርጅቶች በኩልም ለውጦች ታይተዋል፡፡ ዝርዝሩን በዛ ሂደት ውስጥ የተሳተፉ የፓርቲ መሪዎችና ፖለቲከኞች ቢገልፁት የተሻለ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት የሚባለው ጥምረት ሕብረብሄራዊ ብሄራዊ እና የክልላዊ ድርጅቶችን ያቀፈ ሆኖ፣ ውጭ አገር የሚንቀሳቀሱ የሚባሉት ድርጅቶችንም ጨምሮ ተቋቁሞ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ምርጫ 97 መዳረሻ አካባቢ ሕብረ ብሄራዊ የሆኑትና በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱት አራት ድርጅቶች ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ የሚባል አንድ ጥምረት ሲፈጠሩ ሌሎቹ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት ውስጥ ታቅፈው የነበሩት ድርጅቶች እንዳሉ ቀጠሉ፡፡ ምርጫ 97 ላይ በተነሳ የሀሳብና የታክቲክ ልዩነት ህብረቱ ስለተከፋፈለ አሁን አገር ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ ዴሞከራስያዊ ሃይሎች ሕብረት አንድ ሕብረ ብሄራዊ ድርጅት አንድ ብሄራዊ ድርጅት እና አንድ ክልላዊ ድርጅቶችን ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ሕብረ ብሄራዊ ድርጅቶችን ያቀፈው ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ የሚባለው ጥምረት ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት እንደጀመረው ሳይቀጥል ቀርቷል ፡፡

በዚህ ሂደት የታየው ለየት ያለ ክስተት በግለሰቦች ብቻ ሳይሆን በድርጅቶች አባልነትም የተመሰረተ የፓርቲ አደረጃጀት ብቅ ማለቱ ነው፡፡ሕብረብሄራዊ ድርጅቶች ክልላዊ መልክ እና አገርአቀፍ መልክ ይዘው ብቅ ያሉ ሲሆን ኢህአዴግ አገርአቀፉን ኢህዴን በብአዴን ሲተካ በደቡብ ግን ክልላዊ ህብረብሄራዊ ድርጅትን አቀፏል፡ ቅንጅት ሕብረብሄራዊ ድርጅቶችን ሲያቅፍ ብሄራዊ ድርጀቶችን አላካተተም፡፡ በሌላ በኩል ሕብረት ሶስቱንም አይነት ድርጅቶች ባቀፈ መልኩ ራሱን አወቅሯል፡፡ ሌላው ለውጥ ድርጅቶችን አባልና አጋር በሚል ሁለት ደረጃ ያለው ኢህአዴጋዊው ጥምረት ነው፡፡ከዚህ ሁሉ ለመገንዘብ የሚቻለው ትልቁ ቁምነገር አደረጃጀት እንደየሁኔው ሊቀያየር የሚችል ወደ ግብ መዳረሻ የትግል መሳርያ እንጂ የማይነካ የማይለወጥ ሃወልት ነገር አለመሆኑ ነው፡፡ እንደ የመድረኩ ሁኔታ የፖለቲከ ድርጅቶች ይመሰረታሉ፣ ይፈርሳሉ፣ይዋሃዳሉም ይዳቀላሉም፡፡

## 4. የእስካሁኑ ሕብረቶች እና ችግሮቻቸው:-

በገዢው ፓርቲ በኩል እና በተቃዋሚው ሰፈር በኩል የታዩት ህብረቶች የየራሳቸው አካሄድ አላቸው:: በኢህአዴግ ውስጥ እየታየ የመጣው ህብረት ብዙም ውጣ ውረድ ያልታየበት ቀጣይነት ያለው ነበር ማለት ይቻላል:: በተቃዋሚዎች ሰፈር የታዩት ሕብረቶች ግን መፍረስ እና መተባበር የተፈራረቀበት አሁንም ድረስ ስክነት ያላገኘ ሂደት ነው ማለት ይቻላል:: ይህ የሆነው ለምንድ ነው? ምን ልዩ ችግር ቢኖር ነው? ብሎ መፈተሹ ለወደፊት መደረግ ስላለበት አመልካች ስለሆነ ይሄን ጉዳይ መዳሰሱ አስፈላጊ ነው::

ይህ ዳሰሳ ሁሉም ተዋናዬች ሁሉም በዚህ ሂደት የተሳተፉ ፓርቲዎችና የፓርቲ መሪዎች በተሳተፉበት መልኩ ቢካሄድ ጠቃሚ ይሆን ነበር:: ይሄም ሆኖ ግን የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ የሚታየውን ማቅረብ ይፈልጋል::

### 4.1 የኢህአዴግ ሕብረት:-

የኢህአዴግ ህብረት በሂደት ለውጥ እያደረገ ብዙም መፍረስና መሰባበር ያልታየበት ሂደት ነው ሊባል ይቻላል:: ለዚህ ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉት አንዱ ልምድ ነው:: ኢህአዴግ በውስጡ  የፓርቲ አደረጃጀት እና አሰራር በሚመለከት ከሌሎቹ የተሻለ ልምድ ያለው ድርጅት በመሆኑ ይሄ በረጅም ዕድሜ ያካበተው ልምድ እንደ እሴት ጠቅሞታል:: ሁኔታውን እየተከተለ ለውጥ ሲያደርግም ያለ ብዙ ችግር ለውጡን ተግባራዊ ማድረግ አስችሎታል::

ሁለተኛ ምክንያት የኢህአዴግ የዴሞክራሲያዊ ማዕከልነት መርህ ነው:: ይህ መርህ ከጠንካራ የወታደራዊ እዝ ሰንሰለት ብዙም የማይለይ ጠበቅ ያለ ቁጥጥርና የተግባር አንድነት የሚጠብቅ አሰራር ነው:: የሀሳብ ልዩነትን ባለማስተናገድ የውህዳንን መብቶች ባለማስጠበቅ በዚህም ምክንያት በሀሳብ የተለየን በጥርጣሬ ዓይን የማየትና የማግለል ባህርይ ያለው አሰራር በመሆኑ ለአንድ ፓርቲ ህልውና እና ለዴሞክራሲ ትልቅ ሳንካ መሆኑን እውነት ቢሆንም ጨምድዶም ቢሆን ግን አንድን ፓርቲ ለተወሰነ ጊዜ ማስቀጠልና በፓርቲ የተወሰደን  አቋም ማስፈፀም ያስችላል:: ስለሆነም የኢህአዴግ ህብረት እስካሁን ድረስ እንዲዘልቅ አስተዋፅኦ ካደረጉት አንዱ ይህ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ እስከ አሁን ድረስ በድርጅቱ ውስጥ እየተሰራበት ያለው ዴሞክራሲያዊ ማዕከልነት የሚባለው አሰራሩ ነው::

ለዚህ አደረጃጀት መቀጠል አስተዋፅኦ ያደረገ ሶስተኛው ምክንያት ኢህአዴግ ገዥ ፓርቲ መሆኑ ነው:: ሁሉም በእጁ ሁሉም በደጁ ያለለት ስለሆነ ይብላኝ ለተፎካካሪዎቹ እንጂ ለአባሎቹና ለአጋሮቹማ ሜዳው እጅጉን የተመቻቸ ነው::እንጀራ ባለበት ዘመን

ከመጣላት ተስማምቶ መሄድ ስለሚሻል ችግር ቢኖርም ሁላችን የሚያጠፋ ነገር ከምናመጣ ብዙም ሳንገፋፋ ዝም ብለን ብንኖር ይሻላል፣ካልነካሽኝ አልነካህም የሚል አካሄድ እንዲሰፍን አስችለዋል፡፡ ኢህአዴግ ገዢ ፓርቲ ባይሆን እና አሁን ተፎካካሪዎች ያለባቸው ዓይነት ችግር እየገጠመው፣ ለመቀጠል ይቻለዋል ወይ? የሚለው በአወንታ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው፡፡

ኢህአዴግ ፈተና ውስጥ የገባ እለት ሊፈነዱ የሚችሉ ውስጣዊ ቅራኔዎች እንዳሉ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ኢህአዴግ ፕሮግራሙን የሚቀርፀው ፖሊሲዎችን የሚያወጣው ትላልቅ ውሳኔዎቹን የሚወስነው በራሱ በጉባኤ እና በራሱ የአመራር ስብሰባዎች ነው፡፡ አጋሮች በዚህ ሂደት የመሳተፍና የመወሰን ዕድል የላቸውም፡፡ ያም ሆኖ ግን አጋር ተብለው ኢህአዴግ የወሰነውን ፕሮግራም መርሀ-ግብርና ፖሊሲ ቢስማሙበትም ባይስማሙበትም በክልላቸው የማስፈፀም ግዴታ ይጣልባቸዋል፡፡ ለዚህ የሚከፈላቸው ዋጋ ኢህአዴግ በምርጫ ወቅት በክልላቸው እነሱን የማይወዳደር መሆኑን፣ በክልላቸው ያለ ጠንካራ ተፎካካሪ ተመርጠው ስልጣን ላይ የመቀጠል ሰፊ እድል ያላቸው መሆኑ ነው፡፡አጋሮቹ ከአባሎቹ እኩል አለመሆናቸው፣በፖሊሲ ውሳኔዎች ምንም ድምፅ የሌላቸው መሆኑ ውሎ አድሮ ቅራኔ መፍጠሩ አይቀርም፡፡ይህ ቅራኔ አሁን በእህል ውሃ ቢሸፈንም ችግርና ፈተና ሲያጋጥም መነቃነቁ የማይቀርለት ነው፡፡

በኢህአዴግ ኣባል ድርጅቶችም እንዲሁ ለጊዜው በእህል ውሃ ተሸፍኖ የሚሄድ ቀላል ያልሆነ ችግር አለ፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራት ነን አንድ ነን ቢሉም ለኔ ያንሰኛል እገሌ የማይገባውን ይወስዳል የሚል የመሳሳብ ሁኔታ አለ፡፡ ለራስህ ክልል የማድላት አድልዎ ተፈፀመብኝ ብሎ ማጉረምረም የማይቀር ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ዝም አሰኝቶት ሊሆን ይችላል በቀላሉ የማይፈታ ከኢህአዴግ ፀረ-ዴሞክራቲክ ባህርይ አጅጉን የተቆራኝ ችግር መሆኑ ግን ሊጤን ይገባል፡፡

የኢህአዴግ አባል እና አጋር ድርጅቶች በሚያስተዳድሩዋቸው ክልሎች እየታየ ያለው መቋጫ የሌለው የድንበር እና የህዝብ ግጭት ስለኢህአዴግ ብዙ ይናገራል፡፡ የክልል እና የብሄር ስሜትን እየተጠቀሙ ይሄ የኛ ነው እያሉ ተጎራባች ወረዳዎችንና አብረው ለብዙ አመታት የኖሩ ዜጎችን በመሬት በውሃ ነጥብና በሳር የሚያናክሱ ያሉት ማን እንደሾማቸው ይታወቃል፡፡

ሌላውና የዚህ ሁሉ መሳሪያ ሊባል የሚችለው የኢህአዴግ ችግር የዴሞክራሲ ያለ መኖሩ ጉዳይ ነው፡፡ ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ አይደለም፡፡ በእያንዳንዱ ድርጅት ውስጥ አፈና አለ፡፡ ድርጅቶቹ የመሪዎቻቸው እንጂ የአባሎቻቸው አይደሉም፡፡ ዴሞክራቲክ ያልሆነ የድርጅቶች ስብስብ ሊቀጥል የሚችለው ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ አመራር ጉልበት ብቻ ነው፡፡ የዚህ ማሰሪያው ዴሞክራሲያዊ ማዕከልነት መሆኑ

ይታወቃል፡፡ለኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ኢ-ዴሞክራሰያዊነቱ ለድርጅቱ ለራሱ አደጋ እንደመሆኑ ሁሉ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ኢህአዴግን ማስቀጠል አስቸጋሪ ነው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ከስልጣን ቢወገዱ በውስጣቸው ያለው ቅሬታ ፈንድቶ ሊያፈርሳቸው እንደሚችል ስለሚያውቁ እህል ውሃ እንደ ልብ የሚያገኙበትን ስልጣን እንደምንም ብለው ጨምድደው ለመቀጠል ይፈልጋሉ፡፡

መሪዎቹ ኢህአዴግ ከስልጣን ከወረደ የኢትዮጵያ አንድነት ይናጋል ብለው ያስፈራራሉ፡፡ ይህንን የሚሉበት ምክንያት ግለፅ ነው፡፡ ኢህአዴግ ከስልጣን ከወረደ እንደሚፈራርስ ያውቃሉ፡፡ ኢህአዴግ ሲፈራርስ ደግሞ እያንዳንዱ ፈራሽ ድርጅት የየራሱን ክልል ይዞ ሊሄድ ስለሚችል በዚህ ምክንያት አገር ትፈርሳለች ይሉናል፡፡ ግን እነሱ ቢፈርሱ የራሳቸው መዋቅርና ድርጅት ይፈርሳል እንጂ ኢትዮጵያ አትፈርስም፡፡ይህም ሆኖ እኛ ካልገዛን አገር ትበታተናለች ያሉን ሰዎች አገዛዛቸው እንደማይቀጥል ሲያውቁ የመጫወቻ ከርዳቸውን ዋጋ ከፍ ለማድረግ ማንኛውንም ጨዋታ ሊጫወቱ እንደሚችሉ ገምቶ መስራት ይበጃል፡፡

### 4.2 <u>የተፎካካሪ ፓርቲዎች ህብረት እና ችግሮቹ</u>:-

ኢህአዴግን በምርጫ ከስልጣን ለማስወገድ በተፎካካሪዎች በኩል ሙከራዎች መደረጋቸው ቢታወቅም አሁንም ድረስ የሰከነ እና ፋይዳ ያለው ህብረት ዘንድ መድረስ አልተቻለም፡፡ ይልቁንስ አንዱ ሲሞከር ቡዙም ሳይቆይ እየፈረሰ በመታየቱ ህብረት ይፈጠራል የሚለው ተስፋ እየጨለመ መሄዱና በህብረት ጉዳይ ላይ የመሰላቸት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ለዚህ ችግር አንዱ ምክንያት ራሱ በተቃዋሚ ሰፈር ያለ ችግር ነው፡፡ የተወሰኑትን እንመልከት፡፡

<u>ሀ) ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንተባበር ቢሉም ህብረታቸው ከአቋሞች መቀራረብ አይጀምርም</u>፡፡ የአቋም ልዩነቶች እንዳሉዋቸው እየታወቀ እና በነዚህ ዙሪያ ላይ ምን መግባባት እንደተደረሰ ምንስ ልዩነት እንዳለ በአግባቡ ሳይታሽና ሳይታወቅ ነው ህብረት የሚፈጠረው፡፡በብሄር ጥያቄና በኢትዮጵያ አንድነት ዙሪያ ለአስርት ዓመታት የዘለቀ ልዩነት እንዳለ ቢታወቅም በጋራ ቆጭ ብሎ በዚህ ጉዳይ ዙርያ ሊያስማሙ የሚችሉትን ነገሮች አንጥሮ ለመሄድ የሚያስችል ልዩነትን የማቻቻልና አክብሮ የመያዝ ሁኔታ ላይ ለመድረስ አልተቻለም፡፡

በኢኮኖሚ ፖሊሲ ጉዳዬች በተለይ ደግሞ መንግስት በሚኖረው ሚና ላይ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በዚህም ላይ መግባባት መደረሱ እርግጠኛ ሳይሆኑ ወደ ህብረት ቢኬድ ችግር መፍጠሩ አይቀርም፡፡ በህገ-መንግስቱም ዙሪያ ላይ ልዩነቶች አሉ፤እንደዚሁም በትግል ስልት ላይ ልዩነቶች አሉ፡፡ በእነዚህ እና በመሳሰሉት ጉዳዬች ላይ ግልፅ ውይይት አልተደረገም፡፡ የጋራ መግባባት ላይም ተደርሷል ለማለት አስቸጋሪ

ነው፡፡እንደዚህ ባሉ መሰረታዊ ጉዳዬች ላይ ውይይት ተደርጎ የአቋም መቀራረብና የአቋም አንድነት ባልተፈጠረበት ሁኔታ ህብረት ቢፈጠር የቅርፅ ብቻ ነው የሚሆነው እንጂ የይዘት ስለማይሆን ውሎ አድሮ እነዚህ አቋሞች እየገፉ ህብረቱ ለማፈራረስ ምክንያት ይሆናሉ፡፡

ለ) እስካሁን ድረስ የታዩት ህብረቶች በሁኔታዎች አስገዳጅነት የተፈጠሩ እና የአጭር ጊዜ እይታ ብቻ የያዙ ሕብረቶች ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ ምርጫ ሲደርስ የሚቀሰቀሱ ምርጫ ላይ እርስ በርስ ሳይወዳደሩ ኢህአዴግን ለመብለጥና ለማሸነፍ ከሚል ያለፈ ግብ ሳይኖራቸው፤ ኢህአዴግን አስወግዶ በምን ይተካለል የሚለውን የማይመልሱ ጥምረቶች ናቸው፡፡ ይህን የሚያክል ትልቅ ጉዳይ ክፍት ተደርጎ ለሌላ ጊዜ እና ጨዋታ ይተውና አጀንዳው ለአሁኑ አህአድግን እናስወግድ ብቻ ይሆናል፡፡

ሕብረተሰቡ በተቃዋሚዎቹ ላይ «ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ» የሚል ጫና የፈጠረበት ወቅት እንደነበር ይታወቃል፡፡ አንዳንዶቹ ህብረቶች የተፈጠሩት ይህንን ጫና ለማረገብ እንጂ ከመጀመሪያም የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝቦና መፍትሄም አበጅቶ፣ ሰጥቶ ለመቀበል ዝግጁ በመሆን የተጀመሩ ሕብረቶች ነበሩ ለማለት ያስቸግራል፡፡ ይህ በመሆኑ እያንዳንዱ ወገን የየራሱን አቋም እያሰላ የየራሱን ድርጅታዊ ህልውና እያሰበና ለዚህ እየተጨነቀ የሚፈጥረው ህብረት ነው የሚሆነው፡፡

ሕብረት የራሱ ሂደት አለው፡፡ በሂደት እየዳበረ የሚሄድ ኬሚስትሪ አለና በህብረት ውስጥ ይህንን ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ በተለያየ መዋቅር በተለያ አሰራር ውስጥ የነበሩ ኃይሎችን እንዴት  አንድ ጋር ማምጣት ይቻላል የሚለው ነገር በዝርዝር ማሰብና መዘጋጀት ይጠይቃል፡፡ መጀመሪያ በሃሳብ ከዛም በአሰራርና በአደረጃጀት ማቀራረቡና ትግበራውም ጥንቃቄ እና የራሱን ጊዜ የሚጠይቅ የራሱ ሂደት ያለው  ስራ ነው፡፡  በድረስ ድረስ ከተሰራ አለባብሶ ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንደሚባለው ዓይነት ችግር ያስከትላል፡፡

ሐ) ወደፊት ያለመመልከት ችግር አለ፡፡ ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ያለፈውን ፖለቲካል ልዩነታቸው በብስለት ያስተናገዱበት ሁኔታ ባለመኖሩ ይህ መጥፎ ታሪክ የፈጠረው አሁንም ድረስ ያልጠፋ መጥፎ ቁርሾ አለ፡፡ ይህ መጥፎ ታሪክ ወደ አሁኑ ስራ እየመጣ አላስፈላጊ ስሜቶችንና አለመተማመንን የሚፈጥርበትንና በዛሬው ስራ ላይ ዕንቅፋት የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሄ ሳይበቃ ከምርጫ 97 ጋር የተያያዘ በተቃዋሚ  ሰፈር በተፈጠሩት ልዩነቶችና መከፋፈሎች ምክንያት የተፈጠረ አዲስ ሳንካም አለ፡፡ እያንዳንዱ ወገን የየራሱን ስራ ገምግሞ ከዛ ላይ ሊወስድ የሚችለው ጠቃሚ ትምህርት ለሕብረተሰብ ይዞ በመቅረብ ፈንታ አንዱ ሌላውን ጥፋተኛ የሚ ያደርግበትና የሚያወግዝበት ራሱን ነፃ የሚያወጣበት እና ትክክለኛ ነኝ ብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገርበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

ይሄ ትክክለኛ አካሄድ አይደለም፣ እያንዳንዱ ወገን ለዚህ ትግል ሁሉም ተማሪ መሆኑ ተገንዝቦ ካለፈው ትግል ስህተትም እንደተሰራ ተቀብሎ ጣት ከመቀሳሰር ይልቅ ከዛ ስህተት መማርና መውጣት በተገባ ነበር፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲ ነን ባዬች ይህንን ወደኋላ ትተው ወደፊት እያዩ በዋናው የሀገር ጉዳይ ማሰብና ማተኮር ይጠበቅባቸዋል፡፡ይህንን ዳገት ሰይሻገሩ ለአገር የሚተርፍ ቁም ነገር አሰራለሁ፣ እሆናለሁ፣ ማለት የማይታሰብ ነው፡፡

**4.3 ለተግዳረቱ ያለ መመጠን ሁኔታ:-**

በገዢው ፓርቲ በኩል አብዬታዊ ዴሞክራሲ የሚባል የፖለቲካ መስመር አለ፡፡ ይሄ የፖለቲካ መስመር የአንድን ፓርቲ አገዛዝ ለበርካታ ዓመታት ማስቀጠልን ለዚህም ሲባል ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ማጥፋትና ማዳከምን ግድ ይላል፡፡ ይህ መስመር በባህሪው በህገ-መንግስቱ የሰፈረው ስልጣን በነፃ ምርጫ በውድድር በሚገኝ የድምፅ ብልጫ ይያዛል የሚለውንና መድበለ ፓርቲ ስርዓትን  ግድ የሚለውን ህገመንግስታዊ መርህን ይቃረናል፡፡ በኢህአዴግ አብዬታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመርና ኢህአዴግ እቆምለታለሁ በሚለው የኢፊዲሪ ህገ-መንግስት መካከል ተቃርኖ አለ፡፡ ይህ በመሆኑ ኢህአዴግ ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚችለው በህገ-መንግስቱ የሰፈሩት መብቶች በመድፈቅ መሆኑ ተገንዝቦ ሆን ብሎ የዴሞክራሲ ምህዳሩን የሚያጠቡ ህጎችን እያወጣ ነው፡፡ በተፃፉ ህጎችና ባልተፃፉ አሰራሮች አማካኝነት ተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችን የማክሰምና ለነሱ አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ የመፍጠሩ ድርጊት እየተከናወነ ነው፡፡

ተቃዋሚዎች ወይም ተፎካካሪዎቹ በእንደዚህ ያለ ምህዳር ታግለው ለቁምነገር ለመድረስ የሚችሉት ለዚሁ ተግዳረት የሚመጥንና ይህንን ተቋቁሞ ለመዝለቅ የሚችል ጥንካሬ ሲኖራቸው ብቻ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እጅግ የተወሳሰበ መሆኑንም ሊጤን ይገባል፡፡ አስከፊ የሆነ ድህነት አለብን፣ የአካባቢ የፀጥታ ችግር አለብን፣ የውስጥ የፀጥታ ችግሮችና የተወሳሰቡ የሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ ጉዳዬችና ጥያቄዎች አሉብን፡፡ በእንደዚህ ያለ የተወሳሰበ ችግር ያለችን አገር አንድነትዋንና ሰላምዋን ጠብቆ ወደ ተሟላ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ልማት ማሸጋገር ለዚህ የሚበቃ ስክነትና ብስለት ግድ ይላል፡፡

ኢትዮጵያ ይህ ችግር ቢኖርባትም ከዚህ ችግር ለመውጣት በተካሄደው ጉዞ ደግሞ በርካታ መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ዜጎችዋን የያዘው አንድ ትውልድ አጥታለች፡፡ በደርግ ዘመን በተከሰተው ጭፍጨፋና የእርስ በርስ ጦርነት አንድ ትውልድ ጠፍተዋል ተበታትነዋል፡፡ ከዛ ቀጥሎም እንደዚሁ በርካታ መፈናቀልና ስደት ታይተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ሀገራችን በብዛትም በጥራትም ጠንከር ያሉ ፖለቲካል መሪዎች ለማግኘት አልታደለችም፡፡ ይሄ ሳይበቃ በተለያየ ድርጅት የመበታተን ሁኔታ አለ፡፡ ይሄ ራሱ

በፖለቲካ ገበያ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ለተግዳረቱ የማይመጥን አቅምና ብቃት እንዲኖራቸው ምክንያት ሆኖዋል ሊባል ይቻላል።

አንዳንዱ ጋር ሲታይ ፓርቲ መመሰረት ትርፍ ማስገኛ ትንሽ ኩባንያ ወደ መሆን እየወረደበት ሁኔታም ይታያል።ፖለቲከና ፖለቲከኝነት ለሀገር ጥቅም ይበጃል የተባለውን አቋም ይዞ ችግሮችን እየተጋፈጡ ለቁምነገር ማድረስ መሆኑ ቀርቶ ተቃዋሚ ነኝ ብሎ የማሳሳቻ ስራ ለመስራት እንደሽፋን እየሆነ ነው።

ከዚህም አልፎ በአብዛኛው ሊባል የሚችል በተቃዋሚ ሰፈር ዴሞክራቲክ የሆነ የፓርቲ አሰራር ያለመገንባት ችግር አለ። ዴሞክራቲክ ስርዓት እንገነባለን እያሉ በውስጣቸው ግን ዴሞክራቲክ አሰራርና ዴሞክራቲክ ፓርቲ ለመገንባት ያልቻሉ ብዙ ናቸው። ዴሞክራሲ ደግሞ ዴሞክራቲክ ባልሆኑ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው ሊገነባ አይችልም። ዴሞክራቲክ ያልሆነን ስርዓት ዴሞክራቲክ ባልሆነ ፓርቲ አሸንፎ ዴሞከራሲ ላይ መድረስም አይቻልም።

## 5. <u>ህብረት አሁንም ይቻላል</u>:-

ኢህአዴግ የአምስት አመት መርሃ ግብር እያለ በሚያቀርባቸው ሰነዶች ምንም ጠብ የሚል ነገር ሲያጣ «በሁለት አስርት አመታት ውስጥ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካ ላቸው አገራት ተርታ እናሰልፋታለን» የሚል አዲስ መፈክር ይዟል። በሌላ ቋንቋ ልማት እንዳመጣላችሁ ተጨማሪ የሃያ ዓመት ዕድል ሰጡኝ እያለ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢህአዳግ የ17 ዓመት ዕድል ሰጥቶታል። የአለም ዓቀፍ ማህብረሰቡም በሰጠው ፖለቲካዊ ድጋፍ፣ በሰጠው እርዳታ፣ ባደረገው የዕዳ ቅናሽና በሰጠው ብድር ለኢትዮጵያ ያለውን በጎ አመለካከት አሳይተዋል። ይሄም ሆኖ ኢህአዴግ የገባውን ቃል አላከበረም፣ በቃሉም አልተገኘም። ከእንግዲህ ለኢህአዴግ ተጨማሪ ሃያ ዓመት መስጠት ማለት የሃያ ዓመት አፈና፣ የሃያ ዓመት የፍትህ እጦት፣ የሃያ ዓመት የእርስ በርስ ብጥብጥ እና አለመተማመን ማስፈን ማለት ነው።

በኢኮኖሚ ከተመጣም ሌላ የሃያ ዓመት መሞከሪያና መለማመጃ ለመሆን መፍቀድ ማለት ነው። ኢህአዴግ እንኳን ሃያ ዓመትና ሃያ ወርም ሊፈቀድለት አይገባም። ይህንን ማስቀረት የሚቻለው ግን በተባበረ ትግል ብቻ ነው። ተባብሮ በፅናት ከታገሉ የኢህአዴግ ህልም መና ማስቀረት በሱ ምትክ የኢትዮጵያ ህዝብ ህልም ማሳካት ይቻላል።

### 5.1 «<u>ላምባዲና</u>»

ምርጫ 97 በአንድ በኩል ተቃዋሚዎች ተባብረው ሲመጡ ምን ያህል አቅም ሊያሰባስቡ እንደሚችሉ ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ ምርጫ የሚጠይቀው ትብብር የዋዛ እንዳልሆነና በደንብ ያልታሸ ትብብር «የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ» እንደሚሆን በሚገባ አሳይተዋል፡፡

ኢህአዴግ በምርጫ 97 የታየው የህዝብ እንቅስቃሴ በማይደገም መልኩ ለማፈን ምርጫውን ተከትሎ የወሰዳቸው አስደንጋጭና አሳዛኝ ድርጊቶች በሕብረተሰቡ የተውት የስነ-ልቦና ስብራት ቀላል አይደለም፡፡ፓርቲዎችን፣ ፕሬስን እና ሲቪክ ድርጅቶችን አስመልክቶ እየወጡ ያሉት አዋጆች የሚያመለክቱትም የአፈና ዘመቻውን የማስቀጠል፣ የለወጥ ተስፋውን የማጨለም ፍላጎቱ ያልተለወጠ መሆኑን ነው፡፡

ይህም ሆኖ በዚህ ጨለማ ውስጥ የሚታይ ብርሃን አለ፡፡ አንድ ጎልቶ የሚታየው ብርሃን የመስከን ብርሃን ነው፡፡ ከጥላቻና ከስሜት የመውጣት በዚሁ ፈንታ በቁምነገር ላይ የማተኮር አዝማሚያ እየታየ ነው፡፡ ምርጫ 97 የነበረውንና ሁለት ሺ ላይ ያለውን ልዩነት አንድ ጋዜጠኛ በንፅፅር ሲግልጽልኝ « ምርጫ 97 ላይ ማስጮህ በጣም ተፈላጊ ነበር፡፡ ጋዜጣ መሸጥ ላይም ትልቅ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ አንድን ነገር ወስዶ ማስጮህ ከተቻለ ጋዜጣው ሰው ይገዛዋል፡፡ ሁለት ሺ ዓመተ ምህረት ግን ማስጮሁን ህዝቡ አይወደውም ይልቁንስ ስክን ያሉ በቁምነገር ለይ ያተኮሩ በመረጃ ላይ ያተኮሩ ፅሑፋችንና አምዶችን የያዙ ጋዘጦችን ነው አሁን ህዝቡ የሚገዛው አሁን ማስጮሁን እንደማይጠቅመን ስላየን በቁምነገር ላይ በተመረኮዙ ፅሑፎች ላይ እያነጣጠርን ነው»ነበር ያለው፡፡ ይሄ አንድ ምሳሌ ቢሆንም አሁን እየታየ ያለውን የሚገልፅ ምሳሌ ነው፡፡ ይተማመንባቸው የነበረ መሪዎችና ድርጅቶች ምን እንደሆኑ ሲያይ ሕብረተሰቡ ቆም ብሎ ነገሮችን ማየት መጀመሩ እና በቁምነገር ላይ ማተኮሩ ለወደፊት አስተውሎ መሄድን ያመጣልና ይህ ለውጥ ለፖለቲከኞችም ጠቃሚ ነው ለሀገሪቱ የወደፊት የፖለቲካ ጉዞም ትልቅ እሴት ነው፡፡

ውሱን ቢሆንም እየታየ ያለው ሌላው በጎ አዝማምያ በፖለቲከኞች እና በፖለቲካ ፓርቲዎች አካባቢ ያለ ወደ ውስጥ ወደ ራስህ ፍተሻ የመግባት ሁኔታ ነው፡፡ በብዙ ፖለቲከኞች ዓይን ሲታይ ምርጫ 97 በበጎም በመጥፎም ያልተጠበቀ ነገር ነው ያመጣው፡፡ ህዝቡ በጨዋ መንገድ ተመዝግቦ በጨዋነት መብቱን ተጠቅመዋል በዚያን ወቅት ለተከሰተው ውድቀት በህዝቡ ላይ ለማላከክ የሚያስችል ቀዳዳ የለም፡፡ ነገር የተበላሸው በፖለቲከኞች አያያዝ ምክንያት ነው፡፡ይሄ እውነታ ፖለቲከኞችና ፓርቲዎች እኛ ላይ ችግር ሳይኖር አይቀርም ብሎ ወደ ውስጥና ወደራስ እንዲመለከቱ የሚያስገድድ ሁኔታ ተፈጥረዋል፡፡ምናልባትም አካሄድን አጥርቶ ለመሄድ የሚያስችል ጠቃሚ ትምህርት ሊወስድ ይቻል ይሆናል፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ ጎልቶ እየመጣ ያለው ሶስተኛው ነጥብ የመተባበር አስፈላጊነት ነው፡፡ ከዚህ በፊትም የመተባበር ፈላጎት አልነበረም ለማለት ሳይሆን አሁን ግን በሕብረተሰቡም በፖለቲከኞችም ስለመተባበር ሳይሆን ስለትብብሩ ዓይነት ከበፊቱ በተሻለ በፅሞና የማሰብ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ድርጅቶችና ህብረቶች በተናጠል እየወሰኑ ታክቲኮችን በተናጠል በማራመዳቸው ምክንያት የህዝቡ ትግል በተናጠል እየተካሄደ በተናጠል የተመታበት ሁኔታ በመፈጠሩ ሁሉም ተጎጂ መሆኑን እየተገነዘበ የመጣ ይመስላል፡፡ አሁን ደግሞ ኢህአዴግ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በተናጠል መቀርጨፉን ይዟል፡፡ ለተቃዋሚዎቹ አንድ አፋኝ ህግ መድቦላቸዋል፡፡ ለፕሬሱም አንድ አፋኝ ህግ መድቦላቸዋል፡፡ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁ አንድ አፋኝ ህግ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በተናጠል መቀርጨፍ ማለት ይሄ ነው፡፡ እያንዳንዱ ስለ ሌላው አይመለከተኝም እያለ በሄደ ቁጥር ራሱን ለአደጋ እያጋለጠ መሆኑ ሁሉም እየተገነዘበ ነው፡፡ ይህ ዋና ዋና የሚባሉትን የዴሞክራሲ ተቋማትን ለማክሰም እየተካሄደ ያለውን ዘመቻ ማክሸፍ የሚቻለው በጋራ ከተቋቋሙት ብቻ እንደሆነ የመገንዘብ ዕድሉና ጊዜው አሁን ነው፡፡

**5.2 <u>ከሀገር በላይ ነፋስ</u>:-**

የኢህአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እና ልማት ለማምጣት እንቅፋት ከመሆኑ ባሻገር ለሀገሪቱ ህልውናም አደጋ የሆነበት ወቅት ላይ ነው ያለነው፡፡

ኢህአዴግ የፖለቲካ ችግሮችን በውይይት የመፍታት ተግዳረት ሊወጣ ያልቻለ ድርጅት ነው፡፡ ይሄን መቀበል ከራሱ ወንበርና ስልጣን ጋር ስለሚያይዘው በሰላም ሊፈቱ የሚችሉትን ችግሮች ለራሱ ስልጣን ብሎ እያወሳሰበ የፀጥታ ችግር እንዲሆኑ እያደረጋቸው ነው፡፡ ራሱ ሊወጣው ያልቻለ ፖለቲካዊ ተግዳረት ወደ ፀጥታ ችግር አየለወጠ የመከላከያና የፀጥታ ኃይሎች በደማቸው እንዲከፍሉበት እያደረገ ነው፡፡ ይህ የሀገራችን የፀጥታ መደፍረስ ችግር በአካባቢያችን ካለብን የፀጥታ መታወክ ጋር እየተቆራኘ የሀገራችንን ችግር እያወሳሰበ ነው፡፡

ሃገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ በሄር በሄረሰቦች አገር መሆንዋ ታውቆ ለብሄር ብሄረ ሰቦች መብት እውቅና መሰጠቱ ተገቢ ነገር ነው፡፡በዚሁ ረገድ ኢህአዴግ ያደረገው በጎ አስተዋጽኦ መኖሩም አሌ የማይባል ነው፡፡ይህም ሆኖ ግን ድርጅቱ የብሄር ጥያቄን እንደ ለያይቶ መግዣ መሳሪያና ስልት እየተጠቀመበትም ነው፡፡ተጎራባች ህብረተሰቦችና ህዝቦች በይገባኛል ጥያቄ እርስ በርስ የሚጣሉበት እና የሚጋደሉበት ሁኔታ በሃገራችን የተለመደ ክስተት እየሆነ መጥቷል፡፡ በአጠቃላይም በሃገሪቱ በህዝብ ለህዝብ መሀከል ያለው ግንኙነት ደፍርሶ ያለመተማመንና በጐሪጥ የመታየት ሁኔታ እየነገሰ ይገኛል፡፡ እነዚህን እየፈጠረ ያለው ኢህአዴግ ነው ለማለት ባይቻልም መላ ኢትዮጵያን

እያስተዳደሩ ያሉት የኢህአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ከመሆናቸው አንፃር ከደሙ ንፁህ ነን ማለታቸው ማንንም ሊያሳምን አይችልም፡፡

በዚህም ላይ አስከፊ ድህነት አለ፡፡ የአስተዳደር ብልሹነትና የሙስና መንሰራፋት አለ፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮች እየተወሳሰቡና እየተጠላለፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሀገራችንን ህልውና ጥያቄ ላይ እያስገቡት ናቸው፡፡ አገር ሲኖር ስለዴሞክራሲ ስለ ልማት ማሰብ ይቻላል፡፡ አገር የመኖሩ ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ሲገባ ግን መጀመሪያ ከአገር በላይ ነፋስ መባል አለበት፡፡ ለዚህ ተግዳረት የሚመጥን መልስ መስጠት ይጠይቃል፡፡ ይሄ ጉዳይ ቅድሚያ ተሰጥቶት ከዛ በመለስ ያሉት ግንኙነቶችን እንዴት ማቻቻል ይቻላል የሚለውን በፅሞና መመርመር እጅግ አስፈላጊ የሆነበት ሁኔታ ላይ መገኘታችንን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**5.3 <u>የሌላውን እንደራስህ አክብር</u>:-**

የእግዚአብሔር መፅሐፍማ የሚለው ጠላትህን እንደ ራስህ ውደድ ነው፡፡ እያንዳንዳችን ይሄን ብናደርግ የበለጠ ይሆናል፡፡ ይህንን ለማድረግ ባንችል ግን ቢያንስ የሌላውን ወገናችን ሃሳብ እና አቋም ለራሳችን አቋም እና ሐሳብ የምንሰጠውን ያክል አክብሮት መስጠት ይጠበቅብናል፡፡

ህብረት ተመሳሳይ የሆኑ ሃሳቦችን አንድ ላይ እንዲሰባሰቡ ያደርጋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተመሳሳይ አቋምና እምነት ያላቸውን ሰዎች ማሰባሰቢያ መንገድ ነው፡፡ ይሄ ግን ቀላሉ ህብረት ነው፡፡ የህብረት ትልቁ ፋይዳውና ቁምነገሩ የተለያዩትን አንድ ላይ ማምጣት ነው፡፡ የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲቀራረቡ በዚህም ምክንያት የተለያዩ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች በአንድ ጥላ ስር እንዲመጡ ማድረግ ከባዱ ግን ትልቁ የህብረት ፋይዳ ነው፡፡

እዚህ ዘንድ ለመድረስ የሌላውን ሃሳብና እምነት እንደራስህ ማክበር ግድ ይላል፡፡ ይህ መርህ አንዱን የሌላ ወገኑ የሆነው ግን ከራሱ አቋም የተለየውን እምነትና አቋም በአክብሮት እንዲሰማው ይጠይቃል፡፡ መስማትና በጥሞናና በአክብሮት ማዳመጥ የሌላውን ወገንህን ስሞታ ለማወቅ በር ከፋች በመሆኑ ይህ በራሱ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

ከዚህም ባለፈ የሌላውን ወገን የተለየ ሃሳብ ማዳመጥ በርግጥ ልዩነት መኖሩንና ላለመኖሩንም ለመለየት ያስችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በውስጥ አንድነት እያለ ከላይ ያሉት ነገሮች ግን ልዩነት ያለ ያህል ሊያስመስሉ ይችላሉ፡፡ መደማመጥ ካለ ግን በውስጥ የተሸፈኑትን የጋራ እምነቶች ለማግኘት ሲያስችል ዕውነተኛ ልዩነቶችንም ለመለየትና ለማወቅ ያስችላል፡፡ ልዩነት ጫፎች አሉት፡፡ የልዩነቱ የወዲህኛው ጫፍ አለ የልዩነት ወድያኛው ጫፍም አለ፡፡ አንዳንዶቹ ጫፎች ይቀራረባሉና ልዩነቶቹ ቢኖርም የሚቀራረቡትን ጫፎች ለይቶ ለማግኘት መደማመጡ እጅጉን ይረዳል፡፡

ልዩነት እያለም ህብረት ይፈጠራል:: እንደዚህ ያለ መተባበር ፅኑና ዘላቂ ሊሆን የሚችለው መተባበር ባለበት ወቅትም እያንዳንዱ ወገን የሌላኛውን ወገኑን አቋሞችና ስጋቶች ሁል ጊዜ በልቡ ከያዘና ከራሱ እምነቶችና አቋሞች ጋር በልቡ ካስፈረ ነው:: ይህ ካለ በየቀኑ በሚደረግ የጋራ ጉዞ አንዱ የሌላውን ስጋት ግምት ውስጥ እያስገባ እንዲሄድ በዚህም ምክንያት የራስህ ብቻ ሳይሆን የሌላው ወገንህን አቋሞች በሚያጣጥም መልኩ ነገሮችን በየቀኑ ለማስኬድ ዕድል ይሰጣል:: ይሄ ደግሞ የራሱ ፋይዳ አለው::

አንዱ ወገን የሌላኛው ስጋቶችና እምነቶችን በልቡ ሁል ጊዜ እንደሚያስባቸው ከተገነዘበ በመሀከላቸው እምነት ይፈጠራል:: አንዱ በሌለበት ሁኔታ ሌላኛው ሁለቱም ወክሎ ሊሰራ እንደሚችል የጋራ መተማመን ይፈጠራል:: በዚህ ምክንያት ህብረቱ እየጠነከረ ይሄዳል:: እነዚህ ነገሮች ከሌሉ ህብረት የልብና የምር አይሆንም:: ከአንገት በላይ ይሆንና ዞር ካሉ በኋላ የሚፈርስ፣ በመተማመን ላይ ያልተመሰረተ፣ ዘለቄታ የሌለው ይሆናል::

**5.4 <u>የጋራ እሴቶችን ማስቀደም</u>:-**

በሀገራችን ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች የሚጋሯቸው አቋሞችና እምነቶች አሉ:: ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ በኢትዮጵያ ነፃ እና ገለልተኛ ምርጫ እንዲካሄድ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የህግ የበላይነትና የዳኝነት ስርአቱ ነፃነት እውን እንዲሆን፣እውነተኛ የስልጣን ክፍፍል እንዲኖር፣ሲቪል ሰርቪሱና መለዮ ለባሹ ከፓርቲዎች ሸኩቻ ነፃና ገልልተኛ የሃገር አገልጋዮች እንዲሆኑ፣ ይፈልጋሉ:: እነዚህ ትላልቅ የጋራ እሴቶች እንደመሆናቸው በእነዚህ ዙሪያ ተባብሮ በመስራት ረጅም ርቀት ለመሄድ በተቻለ ነበር:: ምናልባትም የተለያዩ ድርጅቶች ስር ለመጠቃለል ምክንያቶች ናቸው ከሚሏዋቸው ልዩነቶች ይልቅ እነዚህ የጋራ የሚባሉ እሴቶቻቸው ሚዛን በደፉ ነበር:: ይህም ሆኖ ግን የጋራ ለሆኑት እሴቶች የሚገባው ክብደት ሰጥቶ በነሱ ላይ መስራትና መቀራረብ ስለሌለ ከህብረት ይልቅ መከፋፈል የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች መለያ ሆኖአል::

በሃገራችን በአላትን አስመልክቶ መግለጫ ወይ ንግግር ሲደረግ ተደጋግሞ የሚሰማ «ይህ በአል ከሌሎች ልዩ የሚያደርገው» የሚል አባባል አለ:: አንድን ነገር ከሌሎች ልዩ የሚያደርገውን መፈለግ እና በዚሁ ላይ የማተኮር አባዜ ከየት እንደሚመነጭና ሰዉ ለምን «ልዩ» ስለተባለው መናገርና ማድመጥ እንደሚፈልግ አይገባኝም:: «እንደ ሌሎች ሁሉ» እያሉ በሌሎቹ እና ባለፉት ላይ ተሞርኩዞ ስለእድገቶች ቀጣይነት ስለነገሮች ተወራራሽነትና ተደጋጋፊነት ከመናገር ይልቅ ልዩነቱን ማድመቅ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ይመስለኛል::

ይህ እውነታ በእርስ በርስ ግንኙነታችንም ላይ ችግር ሳይፈጥር አልቀረም፡፡ በፖለቲከኞች መሀከል ብዙ የማይነገርላቸው የጋራ እምነቶችና እሴቶች እያሉ በልዩነት ዙሪያ መንጠልጠልና መቦጫጨቅ የተለመደ ሆነዋል፡፡ኢትዮጵያዊነታችን አንድ የጋራችን እሴት ነው፡፡ ለዚህ የሚገባው ክብርና ዋጋ ሰጥቶ በዚህ ዙሪያ መተባበር እና መንቀሳቀስ በተገባ ነበር፡፡ ብዙህነታችን ሌላው የጋራችን የሆነ እሴት ነው፡፡ በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ እምነቶች፣ የሚገለጸው ብዙህነታችን ልንሸሸው የማንችል የጋራ ማንነታችን መገለጫ እንደመሆኑ የጋራችን ለሆነው ኢትዮጵያዊነት እንደምንጨነቅ ሁሉ ለብዙህነታችንም የሚገባው ክብደትና ክብር መስጠት ይኖርብናል፡፡

በእነዚህ የጋራችን በሆኑ እሴቶች ላይ ብንመረኮስ እነሱን በማጠናከርና በማክበር መርህ ዙርያ በጋራ ብንሰራ ረዥም ርቀት መሄድ ይቻላል፡፡ ስለህብረት ስናስብ መጀመርያ የጋራ የሆኑትን እምነቶችና እሴቶች ለይቶ በነሱ ዙሪያ መመካከር በነሱ ዙሪያ መግባባት ስለ መፍጠር መሆን አለበት፡፡ በእነዚህ ዙሪያ የሚፈጠረው መግባባትና የጋራ ግንዛቤ ሌሎቹን ልዩነቶችና ችግሮቻችንን እንድናለዝብ፣ እንድንፈታ፣ የሚያስችለን መደገፍያ ምሶሶ ይሰጠናል፡፡ በልዩነት ላይ ማተኮር መደገፊያም ያሳጣል፣ የጋራ መቆሚያንም ይንዳል፡፡ በጋራ እሴቶች የተመሰረተ መደገፊያ ካበጀን ግን ልዩነቶች ሲመጡ ልንቋቋም የሚያስችለን አቅም ይሰጠናል፡፡

### *5.5 <u>ልዩነቶቻችንን እንደተጫራሾች ሳይሆን እንደ ተደጋጋፊ እንያቸው</u>፡-*

አንዳንድ ጊዜ ልዩነቶች በደፈና ልዩነት ተብለው ይቀመጣሉ፡፡ ከዛም አልፎ እንደተጫራሽ ተደርገው ይወሰዱና መግባባት ሳይቻል ይቀራል፡፡

ምርጫ 97 ላይ የግለሰብ መብትና የወል መብት የሚል ክርክር ተነስቶ ነበር፡፡ የወል መብት ተብሎ የተቀመጠው የብሄር ብሄረሰቦች መብት ሲሆን የግለሰብ መብት የተባሉት ደግሞ ሃሳብን የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ የመምረጥ የመመረጥ፣...ወዘተ የመሳሰሉ መብቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ አንድነት እና በብሄር ዙሪያ የነበረው ልዩነት የወል፣የግል የሚል ስም ይዞ ነው ብቅ ያለው፡፡ ከሁለቱ መሃል ቅድሚያ ለማን ይሰጥ በሚል አንዱ ወይ ሌላው ዓይነት ተጫራሽ እንደሆኑ በሚያስመስል መልኩ ነው ክርክሩ ሲካሄድ የቆየው፡፡

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት ግን በሁለቱም መብቶች መሀከል የቻይና ግንብ የለም፡፡ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ኢትዮጵያዊ መሆን እና ከአንድ ኢትዮጵያዊ ብሄር/ብሄረሰብ መወለድ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ ናቸው፡፡ አንዱ ያለ ሌላው አይኖርም፡፡ የግለሰብ መብት ይከበሩ ስንል ኢትዮጵያዊነትን እንደ የወል መለያ ስንወስድ ነው፡፡ በኢትዮጵያዊነት (የወል) ማእቀፍ ስለሚኖር የግለሰብ (የዜግነት) መብት ነው

እየተናገርን ያለነው። የአንድ ብሄር ተወላጆች የብሄር መብት ይከበር ሲባል ያ መብት ሃሳብን በነፃ ከመግለፅ፣ ከመደራጀት፣ ከመመረጥና ከመምረጥ መብት ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። በቋንቋቸው መናገር የሚፈልጉት፣ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ የግለሰብ መብታቸውን እንዲያስከብሩበት ነው። እንደ ግለሰቦች የመደራጀት መብታቸውን እንዲያረጋግጡበት እንደ ግለሰቦች የመምረጥ የመመረጥ መብታቸውን እንዲያረጋግጡበት ነው። በወል መብት ውስጥ የግለሰብ መብት አለ የግለሰብ መብት ማፅቀፍም የወል መብት ነው። አንዱ የሌላው መኖር ግድ ይላልና አንዱን የበላይ አንዱን የበታች፣ አንዱን ቀደምት ሌላውን ሁለተኛ ደረጃ አድርጎ መፈረጅ ዋጋ የለውም። ተደጋጋፊ፣አብሮ ነዋሪ፣ እንጂ ተጫራሾች አይደሉምና።

ይህ ነገር የፖለቲካ ልዩነት ከመሆን አልፎ ወደ አደረጃጀት ልዩነትም ተሻግሮ ቆይቷል። ሕብረ ብሄራዊ እና ብሄራዊ አደረጃጀቶች መገናኛ የሌላቸው ይመስል ለየብቻ ሲሄዱ ቆይተዋል። ኢትዮጵያዊነታችንና ብዙህነታችን ለኛ ተለያይተው ሊኖሩ የማይችሉ የጋራ እሴቶቻችን ናቸው። ትግራዋይ መሆን ኢትዮጵያዊ መሆን ነው። ኢትዮጵያዊ መሆን ትግራዋይ መሆን፣ ኦሮሞ መሆን፣ ነው። አንዱ ያለ ሌላው ራሱን አይገልፅም። አንዱን ሌላውን አጥፍቶ ውይም እንደሌለለ ቆጥሮ ሊሄድ አይችልም። ኢትዮጵያዊነታችንና ብዙህነታችን በየአንዳንዳችን ውስጥ ያሉ አብረው የሚኖሩ ሁለት ንቃተ ህሊናዎች መሆናቸው መቀበል አቅቶን ቆይቷል። ኢትዮጵያዊነት አንድ ንቃተ ህሊና ነው፣ ከእርሱ ጋር አብሮ የሚኖር ትግራዋይነት፣ ኦሮሞነት፣ አማራነት፣ ጉራጌነት፣ ወዘተ እንዳለ መገነዘብ ያስፈልጋል። እነዚህ ንቃተ ህሊናዎች ተጫራሽ አይደሉም እና በአደረጃጀትም ተቆራኝተው ሊሄዱ ይችላሉ። አብሮ ላለመታገልና ህብረት ላለመፍጠር እንቅፋት መሆን አይገባቸውም።

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው በፖለቲካ ሂደት ከሚገኘው ትምህርት እየተወሰደ በአንድ ጫፍ ብሄራዊ ድርጅቶች በሌላ ጫፍ ደግሞ ህብረ ብሄራዊ ድርጅቶች ብቻ ይዘዉት የነበረው ወደ መሀል/አማካይ ስፍራ እየመጣ ነው። ብሄራዊ ድርጅቶችን በአባልነት የተቀበለ አንድ ስብስብ አይተናል። ሕብረብሄራዊ ድርጅቶችን በአባልነት የተቀበለ ሌላ ጥምረት አይተናል። በመሀል ደግሞ ብሄራዊ፣ ክልላዊ እና ሕብረ ብሄራዊ ድርጅቶችን እንደ ድርጅቶች ያጣመረ ትብብር አይተናል። ይሄ እንግዲህ ከትምህርት፣ ከተግባር፣ የደረስንበት መግባባት እንዳለ አመላከች ሲሆን፣ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃም ሁለቱም ንቃተ ህሊናዎች ተጫራሾች አይደሉምና በኃላፊነት መስራት ካለ ተግባር እንዳሳየው ሁለቱም ሞዴል አደረጃጀቶች አማካይ መገናኛ ቦታ አላቸው።

**5.6 <u>አማካይ ስፍራ</u>:-**

ማርክስ ሌኒናዊ ፍልስፍና የሚሽከረከረው በመደብ ትግል ዙሪያ ነው፡፡ በመደብ ትግል ደግሞ አማካይ ቦታ አማካይ ስፍራ የሚባል ቦታ የለም፡፡ ወይ ማሸነፍ ወይ መሸነፍ ነው፡፡ አማካይ ስፍራ መፈለግ የደካማ፣ የፈሪ፣ የወላዋይ፣ ስልት ነው፡፡ ማስታረቅ መሸምገል አንተም ተው አንተም ተው ብሎ ሰጥቶ መቀበል የደካማ ዘዴ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች በዚህ ያለፍን በመሆናችን አንዱ አሸናፊ ሌላው ተሸናፊ ሆኖ መውጣት እንጂ ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት፣ ሁሉም ስጋትና ጭንቀቱ ታይቶለት ፍላጎቱ ተከብሮለት በጋራ ተስማምቶ ወደ ፊት የሚሄድበት ሁኔታ አናይም፡፡

አገራችን ውስጥ ካለው ውስብስብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲከዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ አኳያ በመደብ ትግል ስሌት እየሄዱ በኢትዮጵያ ለውጥ ለማምጣት አይቻልም፡፡ እያንዳንዳችን እኔ ያልኩት ካልሆነ ብለን ገመዱን ወደየራሳችን መንገድ ብቻ ከጎተትነው ይበጠስና ቁርጥራጭ ይዘን እንቀራለን፡፡ ተወደደም ተጠላም እያንዳንዳችን ለሌሎች ፍላጎትና እምነት በውስጣችን በቂ ስፍራ መስጠት አለብን፡፡ ያለዚህ የትም እንደማይደረስ መገንዘብ አለብን፡፡ ይሄ ሲሆን ብቻ ነው ህብረት የሚፈጠረው፡፡

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ በተለይ አማካይ ስፍራ አግኝቶ ሁሉም የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች አንድ ላይ መጣመር ካልቻሉ ኢትዮጵያ የገጠማት ፈተናና ኢህአዴግ እየፈጠረው ያለውን ችግር ተቋቁሞ ዳር መድረስ አይቻልም፡፡ በሌሎች አገሮችና ሁኔታዎች ቢሆን ሁለት ሶስት ጠንካራ የተፎካካሪ ስብስቦችን ይዞ ቁም ነገር መስራት ይቻል ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያ እውነታ ግን አንድ ጠንካራ ተፎካካሪ ስብስብ ተሆኖም ያለውን የፖለቲካ ምህዳር ቀይሮ ኢህአዴግን ከስልጣን ለማስወገድ መቻል ለራሱ ከባድ ስራ ነው፡፡ ስለሆነም በፊታችን ተደቅኖ ያለው ስራ ብዙ ሽግሽግ የሚጠይቅ ሁሉም በተቻለ መጠን ሽግሽግ እያደረገ ሁላችንም የጋራ በምንለው አማካይ ቦታ መገናኘትን ግድ የሚል ስራ ነው፡፡

አማካይ ስፍራ ጋር መምጣት የሚጠይቁት ልዩነቶቻችን የፖለቲከ ልዩነቶቻችን ብቻ አይደሉም፡፡ በሁሉም መስኮች ሽግሽግ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡የሁሉም ተፎካካሪ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች የኢኮኖሚ ፖሊሲ ወደ ካፒታሊስት ኢኮኖሚ መጥተዋል፡፡ ይህም ሆኖ መንግስት በኢኮኖሚ በሚጫወተው ሚና ዙሪያ ልዩነቶች ያሉ ይመስላል፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ምን ማለት እንደሆኑ ምንስ ማለት እንዳልሆነ ተለይተው ባይወጡም አንዱ ሊበራል ዴሞክራሲ ሲል ሌላው ሶሻል ዴሞክራሲ እከተላለሁ ይላል፡፡ በተጨባጭ ወደ ኢትዮጵያ ሁኔታ መጥተው በአንድ የኢኮኖሚ ሴክተር ፖሊሲ ዙርያ ምን ያህል የጎላ ልዩነት እንዳለ በግልፅ አይታይም፣ ሆኖም ግን ይሄ ርእዮተ ዓለም ነው ተብሎ ትልቅ የልዩነት ነጥብ ይሆናል፡፡

በዚህ ምክንያት በተለያዩ ፓርቲዎች መከፋፈል ለኢትዮጵያውያን የፖለቲከ ቅንጦት ነው፡፡አንዱ ከሊበራል ዴሞክራሲ ሌላው ከሶሻል ዴሞክራሲ እየተነሳ በልዩነት ላይ ከማተኮር ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት አስከፊና አሳፋሪ ድህነት አኳያ ምን ብናደርግ ነው የሚሻለን ብሎ ያገርልጅ መፍትሄ መስቀመጥ ነው የሚበጀው፡፡ በአንድ ሴክተር ሊኖር የሚገባው ፖሊሲም በዚሁ መንፈስ ተወያይቶ አማካይ ስፍራ መፍጠር ነው የሚበጀው፡፡

## 5.7 ህገ-መንግስቱን በህገ-መንግስቱ

ህገ መንግስት እንዳለንና በህገ መንግስቱ ዙሪያም የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሉን ይታወቃል፡፡ ያም ሆኖ በህገ መንግስቱ ውስጥ ያሉት መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ማስተካከል የሚቻለው በህገ መንግስቱ መሰረት ለስልጣን ከበቁ በኋላ ነው፡፡ ስለሆነም በህገ መንግስቱ ዙሪያ በተቃዋሚዎች መሀከል ልዩነት እንዳለና እነሱ የሚስተካከሉት ኋላ መሆኑን ተገንዝቦ እስከዛ ድረስ ግን በህገ-መንግስቱ መሰረት ህገ መንግስቱን አክብሮ መታገል እንደሚገባ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል፡፡

ህገ-መንግስቱን ለማሻሻል ይሁን ኢህአዴግን ከስልጣን ለማስወገድ ከሰላማዊ ህጋዊ መንገድ ይልቅ ሌሎች ስልቶችን የሚመርጡ ተቃዋሚዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ህገ-መንግስቱን ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ማሻሻልና ህገ-መንግስቱንም ኢህአዴግንም በሃይል መቀየር የሚሉት የስልት አማራጮች ግን መደበላለቅ የለባቸውም፡፡ የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ የስልቶች መደበላለቅ አላስፈላጊ ችግር ይፈጥራል ብሎ ያምናል፡፡ ከዛም አልፎ ሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ተከትሎ ውጤት ላይ ለመድረስ ይቻላል ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባትም ትክክለኛው አማራጭ ሰላማዊ የትግል ስልት ነው ብሎ ያምናል፡፡በርካታ የኢህአዴግ ተፎካካሪዎች ይህን ይቀበላሉና፣ ይህን የሚቀበሉት ወገኖች መደበላለቁን አስወግደው በዚሁ መንገድ መሄዱ አማራጭ የለውም፡፡

ብዙዎቹ የኢህአዴግ ተፎካካሪዎች በህገመንግስቱ ውስጥ የማይስማሙባቸው አንቀፆችና ጉዳዮች እንዳሉ ሆኖ የሚስማሙባቸው በርካታ ጉዳዬች እንዳሉም ሊጤን ይገባዋል፡፡ እነዛ ሁሉም የሚስማማባቸው ላይ በመመርኮስ በጋራ ብዙ ርቀት ለመሄድ ይቻላል፡፡ በጥሩ ጊዜ የተተከሉ ጠቃሚ አንቀፆች በህገ-መንግስቱ ውስጥ አሉ፡፡ እነዚህ አንቀፆች አሁን ለኢህአዴግ እንቅፋት እየሆኑበት ስለሄዱ የስር ህጎች በማውጣት እነሱን ዋጋቢስ የማድረግ ዘመቻ ይዟል፡፡እንዲህ ባለ ሁኔታ ላይ ያለን መሆኑን በመገንዘብ ተፎከከሪዎች ህገመንግሰቱ ይከበር በማለት ህገመንግሰቱን እየጣሰ ያለውን ኢህአዴግን መታገል እና ማጋለጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ህገ-መንግስቱ አይቀበሉም ብሎ ይከሳል፡፡ ከማንም ተቃዋሚ በላይ የህግመንግስቱ ጠላት ሆኖ ያለው ግን ራሱ ኢህአዴግ ነዉ፡፡ ተፎካካሪዎች ለህገመንግስቱ ያላቸውን አክበሮት በተግባር በማሰየት ወደአጥቂነት መሽጋገር ይኖርባቸዋል፡፡

የመንግስታዊ ተቋማት ነፃነትን በሚመለከት ህገ-መንግስቱ ውስጥ የሰፈሩ ብዙ ጠቃሚ ነገሮች ቢኖሩም በተጨባጭ ግን ነፃና ገለልተኛ ተቋማት የሉንም:: ተፎካካሪዎች ስልጣን ከመያዝ ባሻገር ይህንን እንዲስተካከል የማድረግ ትልቅ ፈተና ይጠብቃቸዋል:: ይህንን ከመንገዱ የወጣውን ነገር ለማስተካከል የሚያስችል ስምምነት ላይ ካልደረሱና ለማስተካከል የሚያስችል በቂ ጊዜ ካልሰጡ ነገሩ ሁሉ ከፈረሱ ጋሪውን ማስቀደም ሊሆን ስለሚችል አስቀድመው ሊያዩትና ሊያስቡበት የሚገባ ነገር ነው::

## 5.8 አርቆ መመልከት

ኢህአዴግን ከስልጣን ማውረድ አንድ ግብ ነው:: ይሄ ከባድ ግብ ቢሆንም በቅርብ ርቀት ያለ ግብ መሆኑ አይቀርም:: ከዛ ባሻገር ብዙ ስራዎችና ብዙ ግቦች አሉ:: ኢህአዴግን ከስልጣን ማውረድ ቢያንስ በምርጫ አብዛኛውን ድምፅ ማግኘት ይጠይቃል:: ይህንን ማሳካት ለራሱ ጠንካራ ትብብር የሚያስፈልገው መሆኑ ቢታመንበትም ይህንን ብቻ እንደግብ የወሰደ ትብብር አይደለም መታሰብ ያለበት:: ይሄ ዓይነቱ ትብብር የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ከሚል ፈሊጥም ሊካሄድ ይችላል:: ይሄን እናሳካና ከዛ በኋላ ላለው ግን ሞያ በልብ ብሎ መሄድ ወደ ችግር መልሶ ሊያስገባ የሚችል በጣም አጭር ግብ ያለው ስልት እንጂ ኢትዮጵያ ላለባት ተግዳሮት የሚመጥን ህብረት አይደለም:: የኢትዮጵያ ችግር ብዙና እጅግ የተወሳሰበ ከመሆኑ ባሻገር ኢህአዴግ ይበልጥ አወሳስቦታል:: ይህንን ችግር ስለመፍታት ስናስብ ኢህአዴግን ማስወገድ ግድ ቢልም ኢህአዴግ ማስወገድን ብቻ እንደ ግብ ይዞ መሄድ በቂ አይደለም:: ከዛ በኋላ በርካታ ፈተናዎችና የተወሳሰቡ ችግሮችን ስለመረከብና ስለማስተናገድ ብዙ ምክክር ይጠይቃል:: ያ ሽግግር በብስለትና በርጋታ ካልተያዘ አገሪቱን በከባድ ችግር ውስጥ ሊከታት እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል:: ስለሆነም የሚፈጠረው ህብረት ከአንድ ምርጫ ባሻገር፣ ኢህአዴግን ከስልጣን ከማውረድ ባሻገር፣ የሚሄድና ከዚያ በኋላ የሚኖሩትን ችግሮች እንዴት እንደሚያስተናግድና እንዴት እንደሚፈታ የሚያስብ፣ረዘም ስላለ የሽግግር ሂደት በቂ ግንዛቤና መግባባት ላይ የደረሰ ህብረት ነው መሆን ያለበት::

ኢህአዴግን እናስወግድ እንጂ ከዛ በኋላ የየራሳችን መንገድና ብልሀት ይለይልን ብለው የሚያስቡ ወገኖች ኢህአዴግ ከተወገደ በኋላ ስለምትኖር ኢትዮጵያ የማይጨነቁና የማይቸገሩ ናቸው:: ኢህአዴግ ተወግዶም በሙሉ የኢትዮጵያ ችግሮች አይወገዱም::ከ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ችግሮች ባሻገር አካባቢያዊ እና ውስጣዊ የፀጥታ ችግሮች እንዳሉን፣ እነዚህ ኢህአዴግን ካስወገዱ በኋላም በቀላሉ የሚጠፉ እንዳልሆኑ እና ገለልተኛ ተቋማት እንደሌሉንም ሊጤን ይገባዋል:: ይሄን ሳያስቡ ከጠባብና አጭር ግብ አኳያ መሰባሰብ ከማይዘልቅ መርከብ ተሳፍሮ ባህር ላይ ሲደርሱ የመስመጥ አደጋ ሊያመጣ

እንደሚችል ጉዞ ነው መታየት ያለበት፡፡የሩቁን ሳያዩ የአጭሩን ብቻ እያዩ መሄድ መጨረሻ ተይታኒክ መሆንን ሊያስከትል ይችላልና፡፡

**5.9 ለአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ፡-**

በኢትዮጵያ በርካታ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ስለእነዚህ ፓርቲዎች ሲወሳ ቀድሞ የሚነሳው የፓርቲው ስም ሳይሆን የመሪው ስም ነው፣ የእንትና ፓርቲ በሚል፡፡ ጠንከር ያለ ፖለቲከኛ ካለ የራሱ ፓርቲ ይኖረዋል ወይም እንዲመሰርት ይጠበቃል፡፡ በዚህ መልኩ በሚቋቋሙት ፓርቲዎች የግለሰቦቹ ባህርያት ሳይቀር ተቋማዊ ህልውና ያገኙና ፓርቲውን ከግለሰቡ ለይቶ ለማየት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ከጠንካራ ግለሰቦች ስብስብ የሚፈጠር ፓርቲ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡አብሮ ለመንገዝ የሚችሉት የእያንዳንዱ ጥቅምና ፍላጎት ሲከበር መሆኑን ሁሉም ስለሚገነዘቡ ፓርቲአቸው ከግለሰብ ባህሪይ እና ፍላጎት ወጣ ያለ ራሱን የቻለ ተቋም እንዲሆን ሆን ብለው ይሰራሉ የመሳከት እድሉም ትልቅ ነው፡፡

በሃገራችን ያሉት ፓርቲዎች እርስ በርሳቸው ተገናኝተው ህብረት ለመመስረት ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡ እስከአሁን ድረስ ለታየው የመተባበር እና ተመልሶ የመፍረስ ሂደት ምክንያት በግለሰቦቹ ላይ ያለ ነው የሚሉ በርካታ ወገኖች አሉ፡፡ መሪዎቹን ለመምራት እንጂ ለመመራት ያልተዘጋጁ ናቸው ብለው የሚተቹም አሉ፡፡ በመሪዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት ሲታይም ከትብብሩ ጥረትና ሙከራ ያተረፉት ነገር ቢኖር እርስ በርስ ያለመተማመን እና አንዱ ሌላውን እንደዚህ ነው ብሎ መፈረጅ ነው፡፡

ይሄም ሆኖ ግን እያንዳንዱ ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ዴሞክራሲ ይጨነቃል፡፡ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ስለ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ መጨነቅ ግን ከራስ መጀመርን ይጠይቃል፡፡ በአንድ በኩል ስለ ኢትዮጵያ አንድነት እየሰበኩ የትብብር ጥያቄ ሲነሳ ግን እንትና እንደዚህ ነው ከእርሱ ጋር መስራት አስቸጋሪ ነው ማለት አንድነትን መውደድ አያመለክትም፡፡ ብዙህነትን ካልተቀበሉ የኢትዮጵያ አንድነትን ማሰብ ይሁን በተፎካካሪዎች መሀከል ስለሚኖር መተባበርን ማሰብ አይቻልም፡፡ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት የሚጨነቅ የኢትዮጵያን ብዙህነት መቀበል ለዚህም አክብሮት መስጠት ይጠይቃል፡፡

በየተለያዩ ፓርቲዎች የተበታተኑ በርካታ ጠንካራ ሰዎች አሉ፡፡ በአንድ ጥላ ካልመጡ ግን ደካማ መሆናቸው አይቀርም፡፡ በተለያየ ጎጆ ከተበተኑት ጠንካራ ሰዎች ይልቅ በአንድ ጥላ ስር የመጡ አማካይ ብቃት ያላቸው ሰዎች ይበልጥ ጥንካሬ ያገኛሉ፡፡ ለዚህም ነው ለአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ የሚለው ምሳሌ ትልቅ ፋይዳ የሚኖረው፡፡

አስር ጠንካራ ሰዎች አስሩም አስር ፓርቲ ላይ ተበተነው አስር ሊቀመንበሮች ከሚሆኑ አንዱን ብቻ ሊቀመንበር አድርገው የቀሩት ዘጠኝ ግን ስራ ተከፋፍለው ቢሰማሩ የበለጠ ውጤት ያለው ስራ መስራት ይቻላል::

እዚህ ላይ መታሰብ ያለበት ነገር ቢኖር የጋራ ቃልኪዳንና ውሉ የመከበሩ ጉዳይ ነው:: አንዱ ሊቀመንበር የሚሆነው ከሌሎቹ ተሽሎ ሳይሆን የጋራ ስራን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግና ለማሳካት አንድ አስተባባሪ ስለሚያስፈልግ፣ ሁሉም አስተባባሪዎች ከሚሆኑ ሌሎቹ በሌላ ስራ ተሰማርተውና ስራ ተከፋፍለው ቢሰማሩ የበለጠ ውጤት ያገኛሉ ከሚል ነው:: በሊቀመንበሩና በሌሎች አባላት መሀከል ያለው ግንኙነት በእኩሎች መሀከል ያለ የስራ ግነኙነት እና የስራ ክፍፍል ነው ተደርጎ መወሰድ ያለበት:: ሊቀመንበር የሆነው ሊቀመንበርነቱን ከልዩ ችሎታ ብቻ ያገኘው፣ ሌሎቹ ሊቀመንበር ሊሆኑ ያልቻሉት ከሊቀመንበሩ ያነሱ በመሆናቸው፣ ከሆነ ወይ እንደዚህ ያለ ግንዛቤ ከተወሰደ ግን ችግር አለ ማለት ነው:: እንደዚህ ያለ ድርጅት ደግሞ ጤነኛ ድርጅት አይወጣውም::ህብረት የእኩሎች ጥምረት፣ የጠንካራ ሰዎች ጥምረት ነው መሆን ያለበት:: በዚህ ስምምነትና ውል ከታሰረ ጉዳዩ አንድን ተልእኮ ለማሳካት የሚደረግ የስራ ክፍፍል ይሆንና መሪዎቹ ሁሉም እንጂ አንድ ብቻ አይሆንም::

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ይሄ ብዙ ያልተለመደ ነው:: መሪ የሆነው ቀስ እያለ ደረቱ ይነፋና፣ ጉልበት ይሰማውና፣ ከሱ ጋር ያሉትን ጠንከር ጠንከር ያሉ ሰዎችን ምክንያት እየፈጠረ ማጥፋትና ማስወገድ ይመጣና፣ የቡድን ስራው እየከሰመ ወደ ግለሰብ አመራር ይቀየራል:: ድርጅቱ በዚህ ምክንያት ይከስማልም ይደክማልም:: ይህ እንዳይሆን የድርጅት ህገደንቦች እና አሰራሮች ስልጣን በአንድ ደረጃ በአንድ ክፍል በአንድ ግለሰብ ለማከማቸት በማይቻልበት መልኩ መቀረጽ ይኖርባቸዋል:: ስልጣንን ለማከማቸትና በርስትነት ለመያዝ የሚቋምጡ ግለሰቦች በወቅቱ ልካቸውን ሊያገኙ የሚችሉበት አሰራር መከተል ይኖርባቸዋል::

አሁን ባለው አካሄድ ኢህአዴግ እጅግ ተመችቶታል:: በማንኛውም የምርጫ ወረዳ ኢህአዴግ አንድ ሆኖ ሲቀርብ ተፎካካሪዎች ግን ከአንድ በላይ ወኪሎች ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ ግን ደካማ አማራጮች ሆነው ነው የሚቀርቡት:: ህዝቡ አማራጭ ቢፈልግም ከኢህአዴግ ውጭ ያሉት አማራጮች ዓይኑን የማይሞሉለት ይሆኑና ሳይወድ ኢህአዴግን ይመርጣል:: አንዳንዴም ከኢህአዴግ ውጭ ያሉ አማራጮች ጥሩ ቢሆኑም ከአንድ በላይ በመሆናቸው በመሀከላቸው ጨረታ ይፈጠርና ሁለቱም ሳይቀናቸው ይቀራል:: ዳገቱን ለመውጣት ጨረታንም ለማስወገድ መተባበር ያስፈልጋል:: በተለመደው የሂሳብ ስሌት የአንድና አንድ ድምር ሁለት ነው:: በመተባበር ግን ድምሩ ከሁለት በላይ ነው የሚሆነው:: በሃገራችን ያሉት የተበታተኑ ደካማ ፓርቲዎች በጋራ

በመስራት አሸናፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ አስበው ለዚሁ የሚከፈለው መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 6. ማጠቃለያ፡-

የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ የማጠቃለያ መልእክት አማካይ ስፍራ እንፍጠር የሚል ነው፡፡ በርካታ የጋራ እምነቶችና አቋሞች እንዳሉን ተገንዝብን ለእነዚህ የሚገባቸው ዋጋና ክብር በመስጠት በእነዚህ ዙሪያ አበክረን እንመካከር አበክረን እንስራ፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ልዩነቶች አሉን፡፡ እነዛ ልዩነቶች እውነት ልዩነቶች መሆናቸውን ለማወቅ ይሁን ምን ያህል የተራራቁ እንደሆኑ ለማወቅ እንድንችል መጀመርያ ቁጭ ብለን እንመካከር ፡፡ ተቀራርበንና ተመካክረን መስራት ከጀመርን ሁላችንንም የሚያስማማ አማካይ የትግል ስፍራ መፍጠር ይቻለናል፡፡ የዚህ አማካይ የትግል ስፍራ መፈጠር ሁሉንም አሸናፊ ያደርገዋል፡፡

የፖለቲካ ልምዳችን በጋራ አሸናፊ ሆኖ መውጣት አላስተማረንም ይልቁንስ ድምሩ ዜሮ የሆነ የፖለቲካ ጨዋታ (zero-sum-game) ያስተማረን በመሆኑ ለኛ ኢትዮጵያዊን በጋራ እምነቶችና ተስፋዎች ዙሪያ ተሰባስቦና ልዩነቶችንም አቻችሎ መሄድ ቀላል ፈተና እንደማይሆን ይገመታል፡፡ይሁን እንጂ ሊያልፉት የማይቻል ፈተና አይሆንም፡፡ይህንን ሳያሳኩ ኢህአዴግን የመተካትና በኢትዮጵያ ድሞክራሲን የማስፈኑን ዳገት መውጣት እንደማይቻል ደግሞ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

ሁኔታው የቆየውን አስተሳሰብና አካሄድ ቀይሮ በአዲስ አስተሳሰብ አዲስ ጉዞ መጓዝ መጀመርን ግድ ይላል፡፡ ይህ ከተሳካ እስካሁን ድረስ ካየናቸው ውጤቶች የተለየ ውጤት ጋር መድረስ ይቻላል፡፡ ካልሆነ ግን የሚደረገው ሙከራ ሰዎች እንደሚሉት አሮጌውን ወይን በአዲስ ጠርሙስ መሙላት ሊሆን ይችላል፡፡